# ተራራው ላይ ያለው መስህብ ምንድን ነው?

እመን ብቻ፡ እመን ብቻ፡
የማይቻል የለም፡ እመን ብቻ።

አሁን ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ።

እግዚአብሔር አባት ሆይ፡ በዚህ ዘመን ለህዝቡ እያደረግኸው ያለኸውን ሁሉ አይተን፡ የዛሬው ከልብ የመነጨ ጸሎታችን ይህ ነው። ጌታ ሆይ፡ የተጻፈው ቃል፡ ለእኛ እየተገለጠ መሆኑን፡ እውነት እንደሆነ ብቻ እንድናምን፡ እንጠይቅሃለን። አባት ሆይ፡ ይህን ይሁንልን።

2 አሁንም ዛሬ በዚህ ጧት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ላበራህልን—ብርሃን እናመሰግንሃለን። ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ በዚህ የጸሎት መሰመር ውስጥ፡ ቃልህ እውነት መሆኑን እንድታረጋግጥልን እንጸልያለን።

3 ከሀገሪቱ ማዶ ጀምሮ እስከ ምዕራባዊው የባሕር ዳርቻ እስከ አሪዞና ተራሮች፡ በ—በ—ታችኛው የቴክሳስ ሜዳዎች፡ እስከ ምሥራቃዊው የባሕር ዳርቻ ድረስ፡ በመላው አገሪቱ በነዚያ፡ ጌታ ሆይ፡ በትናንሽ ማይክሮፎኖች ዙሪያ ለተሰበሰቡት፡ አብያተ ክርስቲያናትና፡ ጉባኤዎች ሁሉ፡ በተሰበሰቡበት ሰፍራ እንጸልያለን። በጊዜ ልዩነት፡ የብዙ ሰዓታት ርቀት ቢኖረንም፡ ነገር ግን፡ ጌታ ሆይ፡ የመሲሑን መምጣት የምንጠባበቅ፡ አማኞች በመሆን፡ ዛሬ ምሽት እንደ አንድ አካል በአንድ ላይ ነን። የሰማዩ አባት ሆይ፡ ለቤተ ክርስቲያንህ እሱን በቶሎ እንድትልከው፡ እንጸልያለን። በሰሙ እንጠይቃለንና። አሜን።

4 አረፍ አረፍ በሉ። ዛሬ ምሽት እዚህ ላላችሁት ሁሉ ክርስቲያናዊ ሰላምታ ይድረሳችሁ። መተንፈስ እስኪያቅተን ድረስ አሁንም በጣም በመጨናነቃችን አዝናለሁ። የአየር ማቀዝቀዣዎቹ እንኳን፡ በጥሩ ሁኔታ ቢሰሩም፡ በሰዎች ብዛት የተነሳ፡ ያን ያህል ተፅዕኖ የላቸውም። በተለመደው መጠን በሰው የተሞላ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ቢሆን ኖሮ፡ እነዚያ የአየር ማቀዝቀዣዎች ያበረዷችሁ ነበር። ሆኖም አሁን እያንዳንዱ ሰው የአየር ማራገቢያ ይዞ፡ እያራገበ ነው፡ የአየር ማቀዝቀዣውም በቻለው አቅም ሁሉ እየነፈሰ ነው።

5 በክርስቶስ ላላችሁና፡ እያዳመጣችሁ ላላችሁ ወዳጆቻችን ሁሉ፡ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ባሕር ዳርቻ ሰላምታ እንልካለን። በሳን ሆሴ ላላችሁት፡ ለወንድም ቦርደርስ፡ በዚያ ላለውም ቡድን ሰላምታ እንልካለን። ሰላምታ በአሪዞና፡ ፕሪስኮት፡ ተራሮች ላይ ለሚገኘው፡ ለወንድም ሊዮ መርሲየርና የጌታን መምጣት በዚያ ለሚጠባበቀው ቡድኑ ሰላምታ እንልካለን። ዛሬ ምሽት ተሰብሰበው፡ የጌታን መምጣት ለሚጠባበቁት፡ በቱክሰን ላሉት ሰላምታችን ይድረሰ። በቴክሳስ፡ ሂውስተን ውስጥ፡ የጌታን መምጣት ለሚጠባበቁት። በቺካጎ፡ የጌታን መምጣት ለሚጠባበቁት። በምሥራቃዊው የባሕር ዳርቻ፡ በኒው ዮርክና በኮነቲከት፡ የጌታን መምጣት ለሚጠባበቁት፡

በዚያ ለሚገኙ ብዛት ላላቸው ወገኖች። እዚህ እነሱን ለማስቀመጥ የሚያስችል በቂ ስፍራ የለንም፡ ስለዚህ በ—በስልክ መስመር አማካኝነት ቃሉን ልንልክላቸው ይገባል። ዛሬ ምሽት ለወንድም ጁኒየር ጃክሰንና፡ በክላርክስቪል ላለው ቡድኑ ሰላምታ እንልካለን። በ62 ላይ ላለው፡ ወንድም ሩዴልና፡ የጌታን መምጣት ለሚጠባበቀው ቡድኑ፡ ሰላምታ ይሁን። ዛሬ ምሽትም በዋናው ቤተ ክርስቲያን፡ በተበርናክል፡ የጌታን መምጣት እየተጠባበቅን እዚህ ተሰብስበናል።

6 አሁንም፡ ብዙዎቻችሁ ምናልባት በዛሬ ጠዋቱ አገልግሎት ላይ ያልነበራችሁ ይሆናል። ነገር ግን ያልነበሩት ሁሉ፡ ቅጂውን እንደሚያገኙ፡ ተስፋ አደርጋለሁ፡ ምክንያቱም ለቤተ ክርስቲያን የተላለፈ እጅግ ቀጥተኛው መልእክት እንደነበረ አምናለሁና—**ጌቶች ሆይ፡ ስንት ሰዓት ነው** ከሚለው በመቀጠል? የመንፈስ ቅባት ተሰማኝ፡ የተናገርኩትንም ለመናገር የተመራሁ መሰለኝ። ረጅም ነበረ፡ ቢሆንም እንዳደርገው ምሪቱ ተሰምቶኛል። ጌታም በቃሉ፡ በምን ዓይነት ሰዓት ላይ እየኖርን እንዳለን፡ እንዳሳየን አስባለሁ። እየሆኑ ያሉትንም እነዚህን ምስጢራዊ ነገሮች መረዳታችንን እርግጠኞች እንሁን። መጽሐፍ ቅዱስ፡ “ጥበበኞች ያስተውላሉ” እንዳለ፡ ታውቃላችሁ።

7 ነገር ግን ሕዝቦችና መንግሥታት “ደካማና ብልህ” እየሆኑ ይሄዳሉ። እስኪ አስቡት፡ አሁን በአማካይ አሜሪካዊ በመካከለኛ ዕድሜ ላይ ይገኛል፡ ዕድሜውም ሃያ ዓመት ገደማ ሲሆን፡ ደካማ ነገር ግን ብልህ ነው። በዚያ ዘመን የጄት አውሮፕላኖች፡ እ—እና የአቶሚክ የጦር አረሮች አልነበሯቸውም፡ ነገር ግን እጅግ ረጅም ዕድሜ ይኖሩ ነበር። እኛ ደካሞችና ብልሆች እየሆንን ነው፡ ሊያጠፋንም ያለው የራሳችን ጥበብ ነው። ራሳችንን እናጠፋለን። እግዚአብሔር አያጠፋንም፥ የራሳችን ጥበብ ያጠፋናል። ሁልጊዜም እንዲሁ ነበረ፡ አሁንም እንደገና እንዲሁ ይሆናል።

8 አሁን፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ በሚቀጥለው እሑድ ጠዋት፡ በምን ላይ እንደምሰብክ በአሁኑ ሰዓት ባላውቅም፡ ነገር ግን ጌታን በመታመን፡ በሕይወት ካቆየንና፡ ምንም ነገር ሳይከሰት ፈቃዱም ቢሆን፡ በሚቀጥለው እሑድ ጠዋት ሌላ መልእክት ለመናገር፡ በሚቀጥለው እሑድ ምሽትም ለሕሙማን ለመጸለይ አስበናል። ከዚያም ልጆቹ በትምህርት ቤት እንዲመዘገቡ፡ ቤተሰቤን ይዤ ወደ አሪዞና ወደ ቤቴ መመለስ ይኖርብኛል። ከዚያም እ... ስብሰባዎቹ፡ ሲቃረቡ፡ ወይም ልንገኝባቸው ስላሰብናቸው ቦታዎችና... ጊዜያት፡ በቻልነው ፍጥነት እናሳውቃችኋለን። ስለዚህ፡ እግዚአብሔር ሁላችሁንም ይባርክ።

9 አሁን ዛሬ ምሽት፡ እንደተረዳሁትም... ለመጀመር ያህል፡ አሥራ አምስት ደቂቃ ያህል እንደዘገየሁ፡ እዚህ በጄፈርሰንቪል ከምሽቱ ሩብ ጉዳይ ለሰምንት ሲሆን፥ ይህም በምሥራቅ ዳርቻ ሩብ ጉዳይ ለዘጠኝ ገደማ ነው፡ ከዚያም በምዕራብ ዳርቻ ከቀኑ አስራ አንድ ሰዓት ገደማ ነው። ስለዚህ አሁን እዚህ ፀሐይ ልትጠልቅ አካባቢ ነን። የመንፈስ ቅባትን ለማግኘት በመሞከር፡ ለአጭር ጊዜ ብቻ ላናግራችሁ እፈልጋለሁ፡ ከዚያም የጸሎት መስመሩን እጠራለሁ።

10 እዚህ ያለውን ጉባኤም ሆነ፡ በሌሎች ቦታዎች የተሰበሰቡትን ጉባኤዎች፡ በመንፈስ የተቀባ አንዳንድ ሰው፡ አንዳንድ ወንድም እንዲያዘጋጁ እፈልጋለሁ፥

ለሕሙማን መጸለይ ስንጀምርም፡ በጉባኤያችሁ ውስጥ ባሉት ላይ እጃቸውን ይጫኑባቸው። አስታውሱ፡ እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ የሚገኝ ነው፥ በሁሉም ስፍራ አለ። ስለዚህ፡ በቴክሳስ ውስጥ፡ በካሊፎርኒያ፡ በአሪዞና፡ የትም ብትሆኑ፡ ለታመሙ ሰዎች ስንጸልይላቸው በታመሙት ላይ እጃችሁን ጫኑ። እኔም እግዚአብሔር እንደሚሰማና የጸሎት መልስ እንደሚሰጥ እርግጠኛ ነኝ።

11 የሚገርም ነገር ነው፡ ባለፈው እሑድ ምሽት፡ ቅባቱ ቀጥሎ ነበር፡ መንፈስ ቅዱስም... በጣም የሚያስገርም ነበር። ከዚህ በፊት እዚህ ከነበርኩበት ጊዜ ጀምሮ፡ ለብዙ ወራት ያህል ምንም ዓይነት የ—የመለየት መርሃ ግብር አልነበረኝም። ከዚያም እንደዚያ ዓይነት ተሰፋ ገብቶ ወደዚያ መውጣት... እርሱ እንደሚፈጽም አታውቁም። እርግጠኛ መሆን አትችሉም። ዝም ብላችሁ ወደዚያ ወጥታችሁ መጠበቅ ብቻ ነው ያለባችሁ። እርሱ ሉዓላዊ ነው። የወደደውን ያደርጋል። ሆኖም ምን እንደሚያደርግ ለማየት በዚያ መቆምና መጠበቅ፡ ከዚያም በእናንተ ላይ እንደዚያ ሲያልፍ መሰማት አለበት።

12 በ—በስብሰባው ፍጻሜ ላይ፡ ማን እንደነበረ አላወቅኩም ነበር፡ ሆኖም በመስመሩ የ—የሆነ ቦታ ላይ ረጅም ይሆን፡ እናቱ ላይ ራስ በራ የሆነና፡ እጅግ የታመመ አንድ—አንድ ሰው ነበረ።

13 በመጨረሻም ላይ፡ አንድ ሰው እዚህ መድረክ ላይ ታየ፡ ራሱን ዝቅ አድርጎ፡ እየተሰቃየ ይመስል ነበር፡ ሆዱንም ይዞ ነበር። ያ የመጀመሪያው ወይም ሁለተኛው ሰው፡ ወይም መቼም ቢሆን የጸለይኩለት እርሱ መሆን አለበት ብዬ አሰብኩኝ፡ ምክንያቱም ራስ በራ ስለነበረና ራሱን ዝቅ አድርጎ የያዘ፥ ግዙፍ፡ ጎበጥ ያለ ሰው ነበር። ሆኖም ዙሪያዬን ተመልክቼ ጨዋውን ሰው እዚያ ተቀምጦ አገኘሁት፡ ነገር ግን እርሱ ደስ እያለው ነበር። “የት አለ፡” ብዬ አሰብኩኝ? ይኸው እዚህ አለ ለማለት አልቻልኩም ነበር። ሊሰማኝና በፊቴ ያለውን ሰው ማየት እችል ነበር።

በዚህ በኩል ትኩረት ሲሰብ ተሰማኝ፡ መሰህቡም ከበስተጀርባ ነበር። ወንድም ኔቪልንና እዚህ የተቀመጡትን ሁለቱን አየሁ፡ እነርሱ ግን አልነበሩም። “ሰውየው እዚያ በስተጀርባ ባለው የጥምቀት ገንዳ ውስጥ ነው ያለው፡” አልኩኝ። ማን እንደነበረ ታውቃላችሁ? ወንድም ሼፐርድ ነበር። ልለየው ያልቻልኩበት ምክንያት፡ ራሱን ቀብሮ እዚያ በጀርባ ተቀምጦ፡ ይጸልይ ስለነበር ነው።

14 የሚሞት መስሎት ነበር፡ ላለፉት ጥቂት ሳምንታትም እንዲሁ አስቦ ነበር። ሚስቱ አዲስ ጫማ እንዲገዛ ስትነግረው፡ እርሱ ግን፡ “አያስፈልጉኝም። ያን ያህል ጊዜ እዚህ አልቆይም” አላት።

15 በቀደም በወንድም ዉድ ግቢ ውስጥ... እዚያ ላይ አገኘኝ፡ ወንድም ውድ፡ እየጮኸና እግዚአብሔርን እያመሰገነ ነበር። “ቤከን፡ ዕንቁላል፡ ቲማቲም፡ የምፈልገውን ማንኛውንም ነገር እየበላሁ ነው፡” አለኝ።

16 በታላቅ ትሕትናም ወንበሩን ትቶ፡ ከመንገድ ዘወር ብሎ፡ በዚያ በስተጀርባ ጸለየ። አያችሁ፡ የጸሎት ካርድ አያስፈልጋችሁም፡ እምነት ብቻ ነው የሚያስፈልጋችሁ። አያችሁ?

አሁን፡ እርሱ መፈወሱን ወይም አለመፈወሱን አላወቅኩም ነበር፡ ዝም ብዬ፡ “አንድ—አንድ ሰው፡ እየጸለየ ነው፡ የሆነ ችግር አለበት” አልኩኝ።

ምን እንደነበረ የጠራሁት ይመስለኛል፥ “የሆድ ሕመም፡ እዚህ በስተጀርባም እየጸለየ ነው። ጌታ ኢየሱስ ያድንህ።” አሁን፡ ማለት የቻልኩት ያን ብቻ ነበር። ስህበቱ እርሱ ይጸልይ የነበረ መሆኑ ነው። ማየት ችዬ ነበር፡ ነገር ግን ምን እንደተፈጠረ አላውቅም ነበር። አያችሁ?

17 ሆኖም ተመልሶ ሲመጣ ስትሰሙት፡ “**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡**” ሲል፡ ሁሉም ሰው ይገነዘባል፡ አያችሁ፡ ከእንግዲህ የምናገረው ራሴ አይደለሁም፥ እርሱ ነው እንጂ።

18 ነገር ግን ሁልጊዜም፡ “ኢየሱስ ክርስቶስ ፈውሶሃል” እላለሁ፡ ይህ በትክክል እውነት ነው። “እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፡ በእርሱ ቍስል እኛ ተፈወስን።” አያችሁ? አያችሁ?

19 ሆኖም “**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፡” ከሆነ፡ እና ምን ማድረግ እንዳለባችሁና ምን እንደሚሆን ሲነግራችሁ፡ ያንን ተከታተሉ፡ ልክ እንደዚያው ይሆናል።

20 እንዲህ ካልኩኝ ግን፡ “ኢየሱስ ክርስቶስ ፈውሶሃል ጤነኛም አድርጎሃል” በምልበት ጊዜ፡ እመኑት፡ ምክንያቱም እርሱ አስቀድሞ ተናግሮታል። እኔ እርሱ የተናገረውን ደግሜ እየተናገርኩኝ ብቻ ነው።

21 ራዕይ ደግሞ እሱ ያሳየውን መድገም ብቻ ነው። ገባችሁ?

22 አሁን ቶሎ ብለን ወደ ቃሉ እናልፋለን፡ ምክንያቱም ብዙዎቻችሁ እዚህ ያላችሁ ሁሉ፡ ዛሬ ማታ ለመጓዝ ረጅም ርቀት እንደምትሄዱ አውቃለሁ። እግዚአብሔር እንዲባርካችሁ፡ በመንገድ ላይም እንዲጠብቃችሁ እጸልያለሁ። እና አሁን ዛሬ ማታ በቅዱስ ማቴዎስ፡ 21 ኛው ምዕራፍ፡ ከ 1 እስከ 11 ላይ ያለውን፡ እንድትከፍቱ እፈልጋለሁ። እና፡ አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ከሌላችሁ፡ ወይም እነዚህን ቅዱሳት መጻሕፍት መጻፍ ከፈለጋችሁ፡ መልካም ነው።

23 አሁን ዛሬ ጠዋት መልእክቱን ላልሰማችሁትና፡ የቴፕ መቅረጫ ላላችሁ፥ እኛ ካሴቶችን ለመሸጥ በጭራሽ አንለምንም፡ ማንኛውንም ነገር ለመሸጥ አንለምንም። አንዳንድ ጊዜ በትልልቅ ሰብሰባዎች ላይ በስተጀርባ መጻሕፍት እንዳሏቸው ያስታውቃሉ፥ እኛ ከእነርሱ ምንም ዓይነት ትርፍ አናገኝባቸውም። ወንድም ቬይል ጸሐፊው ነው። ካሴቶቹን በተመለከተ፡ በዚያ የካሴት ሥራውን የሚያንቀሳቅሰው ሰው ይነግራችኋል፡ እኛ ከካሴት ሽያጭ ምንም ገንዘብ አናገኝም። እኛ እ... ነገሩ ስለ “ካሴቶቹ” አይደለም፥ ስለ መልእክቱ ነው እንጂ። አንድ ሰው በአእምሮው ውስጥ ስለ ገንዘብ ብቻ ካሰበ፡ ከእንግዲህ ካሴቶችን አይቀዳም። ያ ትክክል ነው። ስለ ጉዳዩ እየጠየቅኩኝ ነበር፡ ካሴቶቻችን፡ ከአምስት ዶላር በታች፡ ወይም፡ ከሦስት እስከ አምስት፡ ወይም ወደዚያ አካባቢ እንደሚሸጡ አስባለሁ። ምን አሉ? ሦስት፥ ለነዚያ፡ ትላልቅ ረጅም ካሴቶች ደግሞ፡ አራት ዶላር።

24 ስለ የአንድ አገልጋይም በተመለከተ፡ ስለ አንዱ ካሴቱ ጠይቄ ነበር፡ እርሱም ወደ ሃያ ወይም ሠላሳ ደቂቃ ያህል ለሚሆን፡ መልእክት፡ ዘጠኝ ዶላር ነበረ።

25 ስለዚህ በጀርባ ያለው ወንድማችን ሶትማንም ሆነ፡ ከእነርሱ ማናቸውም፡ እነዚህን በ—በሚያወጧቸው ካሴቶች እየበለጸጉ አለመሆናቸውን እረዳለሁ።

እያችሁ፡ የሚያገኙት ለመኖርያ የሚበቃቸውን ያህል ብቻ ነው። በነጻ እንዲቀዱልን ልንጠይቃቸው አንችልም፡ ምክንያቱም ካሴቶቹንና ሌላውን ነገር ሁሉ መግዛት አለባቸውና። ማሽነሪዎቹም በጣም ውድ ናቸው፡ ለመጀመርያ ያህል፡ እነዚያን ካሴቶች ለመቅዳት ዝግጅቱን ለማድረግ ወደ አሥር ሺህ ዶላር ገደማ ያስወጣል።

26 አሁን፡ በቅርቡ እንደተረዳሁት... እስካሁን ይፋ አላደረግኩትም። ነገር ግን እንደገና ቴፕ መስማት አለ። ሁልጊዜም እኛ... ባለ አደራዎች፡ ከእሱ ጋር ምንም ግንኙነት የለኝም። በየትኛውም ስብሰባ ላይ እንኳ አልገኝም... በጭራሽ። ደ— ደጋፊም ሆነ ተቃዋሚ አይደለሁም። እነርሱ ጨረታቸውን ያቀርባሉ፥ ባለ አደራዎች ቀጣዩ ካሴቶችን የሚቀዳው ሰው ማን መሆን እንዳለበት ይወስናሉ፡ ደብዳቤም ይልኩለታል። ስለ እሱ የማውቀው ይህን ብቻ ነው። እነርሱ ያንን ሰራቸው ነው፡ ምክንያቱም ካሴቶችን መሰራት ይቅርና፡ ሕፃናትን አደራ መሰጠት፡ ወይም ማጥመቅም አልችልም።

27 ስለዚህ አእምሮዬን በዚህ መልእክት ላይ እንዲያተኩር አድርጌዋለሁ፡ ይህም ያ ሦስተኛው ሰህበት ነው፡ ታማኝና ቅን ልሆንለት የሚገባኝም ለእሱ ነው።

28 ማቴዎስ 21፡1 እስከ 11። ያንን ያልኩት ወደ... መጽሐፍ ቅዱስ እንድትመለሱ ለመጠባበቅ እንድትችሉ ነው።

> ወደ... **ኢየሩሳሌምም ቀርበው፡ ወደ ደብረ ዘይት ተራራ፡ ወደ ቤተ ፋጌ በደረሱ ጊዜ፡...** ኢየሱስ **ከደቀ መዛሙርቱ ሁለት** ላከ፡
>
> **እንዲህም አላቸው፡ በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ፡ በዚያን ጊዜም የታሰረችን አህያ፡ ውርንጫም ከእርሰዋ ጋር ታገኛላችሁ፥ ፈትታችሁ፡** ወደ **እኔ አምጡልኝ።**
>
> **ማንም አንዳች ቢላችሁ፡ ለጌታ** ያስፈልጉታል፡ **በሉ፥ ወዲያውም ይሰዳቸዋል።**
>
> ይህ ሁሉ **የሆነው፡ በነቢዩ፡ እንዲህ ተብሎ የተነገረው ይፈጸም ዘንድ ነው፡**
>
> **ለጽዮን** ሴቶች ልጆች **ንገሯቸው፡ እነሆ፡ ንጉሣችሁ የዋህ ሆኖ፡... በአህያ ላይና በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ፡ ወደ እናንተ ይመጣል።**
>
> **ደቀ መዛሙርቱም ሄደው፡ ኢየሱስ እንዳዘዛቸው አደረጉ፡**
>
> **አህያይቱንና፡** ው—ውርንጫዋንም **አመጡለት፡ ልብሳቸውንም በእነርሱ ላይ ጫኑ፡ ተቀመጠባቸውም።**
>
> **ከሕዝቡም** እጅግ **ብዙዎች ልብሳቸውን በመንገድ ላይ አነጠፉ፥ ሌሎችም** ከዛፍ **ጫፍ ጫፉን እየቈረጡ፡ በመንገድ ላይ** ያነጥፉ **ነበር።**
>
> **የሚቀድሙትም** ሕዝብ፡ **የሚከተሉትም፡ ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ፡ በጌታ ስም የሚመጣ፡ የተባረከ ነው፥ ሆሣዕና በአርያም፥ እያሉ ይጮኹ ነበር።**

**ወደ ኢየሩሳሌምም በገባ ጊዜ መላው ከተማ፡ ይህ ማን ነው፡ ብሎ፡ ተናወጠ?**

**ሕዝቡም፡ ይህ ከገሊላ ናዝሬት የመጣ ነቢዩ ኢየሱስ ነው አሉ።**

29 አሁን ከዚህ ርዕስ ልወስድ ብል፡ የጸሎት መስመሩ ከመጀመሩ በፊት ወደ ሠላሳ ደቂቃ ያህል፡ ይህንን ርዕስ መውሰድ እወዳለሁ፥ **ተራራው ላይ ያለው መሰህብ ምንድን ነው?**

30 ያኔ፡ በጣም አድካሚና፡ አስጨናቂ ቀን ነበረ፡ ያልተለመደ ቀን። እዚህ ጋር ኢየሱስ ፋሲካን ለማክበር ተዘጋጅቶ፡ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ እናየዋለን። ፋሲካም የፋሲካ በግ የሚታረድበት፡ ደሙም ለሕዝቡ ማ—ማስተሰረያ—ለሕዝቡ በስርየት መቀመጫው ላይ የሚረጭበት ነበር። እርሱም ከቤተ ፋጌ ወጥቶ ወደ ደብረ ዘይት ተራራ ራስ መጥቶ ነበር፡ ይህም ኢየሩሳሌም ከተገነባችበት ሌላ ትንሽ ኮረብታ ላይ ሆኖ ወደ ታች ተመለከተ። እየተመለከተም፡ ይህ የመጨረሻ ጉብኝቱ እንደሆነ ያውቅ ነበር።

31 ይህም ኃጢአተኞች በሆኑ ሰዎች እጅ አልፎ የሚሰጥበትና እነርሱም እርሱን የሚገድሉበት ጊዜ ነበረ። በሟች ሰው ሊሞት ከሚችለው ሁሉ እጅግ አስከፊውን ሞት ሊሞት፡ ሊቀበርም ነው። ከእርሱ ጋር አብረው በቆሙት፡ በገዛ ወገኖቹ ተላልፎ ይሰጣል። እርሱም፡ አምላክ በመሆኑ፡ በልባቸው ያለውን ያውቅ ነበር፡ ማን አሳልፎ እንደሚሰጠውም ከመጀመሪያው ያውቅ ነበር። በአጠገቡ ተቀምጦ ገንዘቡን የቆጠረለትና፡ ሌሎችም ነገሮች ያደረገለት ያ ሰው፡ አሳልፎ እንደሚሰጠው ያውቅ ነበር። ጨካኝ የሮማውያን መስቀል በዚያ እንደሚጠብቀውም ያውቅ ነበር። በሰውነቱ ውስጥ ያለው ውሃና የሰውነቱ ደም እንደሚለያዩ ያውቅ ነበር፡ ደሙም እንደ ላብ ያሉ ትላልቅ ጠብታዎች ሆኖ፡ ከግንባሩ እንደሚንጠባጠብ ያውቅ ነበር። በፊቱ ያለውን ይህንን ሁሉ ያውቅ ነበር። በተራራውም ላይ ቆሞ፡ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለከተ።

32 የዚያ ዘመን ሰዎች፡ በ... በዚያ ዘመን፡ "የተሻለ ሃይማኖተኛ የኅብረተሰብ ክፍል" ብለው የሚጠሯቸው፡ ጠሉት። የዚያ ዘመን አብያተ ክርስቲያናት ይጠሉትና ያወግዙት ነበር፡ እርሱን የሚሰሙትንም ሁሉ ያወግዙ ነበር። ሄደውም በአገልግሎቶቹ ላይ ከተሳተፉ፡ ወዲያውኑ ከቤተ ክርስቲያን ኅብረት ይወገዱ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ "ወደ ገዛ ወገኖቹ መጣ፡ የገዛ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም፡" ማለቱ አያስገርምም። ሊወዱት የተገባቸው፡ ከእርሱ ጋር ሊሆኑ የተገባቸው፡ የእርሱ መራራ፡ እጅግ በጣም መራራ ጠላቶቹ ሆኑ።

33 እርሱም ትንሹን ቡድኑን ያቋቋመው ከድሆች ሕዝብ፡ ከአሳ አጥማጆች፡ ከቀረጥ ሰብሳቢዎች፡ ካልተማሩት ሰዎች ነበረ። መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንዶቹ እንዲያውም "ያልተማሩና፡ መሃይም" እንደነበሩ ይናገራል። አንዳንዶቹ ስማቸውን እንኳ መጻፍ አይችሉም ነበር። እርሱ ህዝቡን ለማግኘት ብሎ ወደ አብያተ ክርስቲያናት በጭራሽ አልሄደም።

34 ከማናቸውም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር ፈጽሞ አልተስማማም ነበር። ከዚያም፡ በተጨማሪ፡ የነቢይን ፈለግ በትክክል ተከተለ። ከእርሱ በፊት የነበሩት እንዳደረጉት ሁሉ፡ እርሱም ያደረጉትን ነገር ሁሉ አወገዘ፥ ምክንያቱም እነዚያ ቃሉን በከፊል የነበሩ ሲሆኑ፡ እርሱ ግን ቃሉ በሙላት እርሱ ነበረ።

35 በዚህ ሁሉ መካከል ግን፡ ከዚህ በፊት በነበሩትም ሆነ በመጡት በየዘመኑ በተነሱት ነብያት አማካኝነት፡ ያንን መልእክት እንዲሰሙ አስቀድመው የተወሰኑ ሰዎች ይኖራሉ፡ እነርሱም ይከተሉታል። እነርሱም ብዙሐኑን ችላ ይላሉ። የማያምኑትን ሰዎች ትችት ችላ ይላሉ። እ—ከእነርሱ ጋር አይከራከሩም። የሚያደርጉት አንድ ነገር ብቻ ነው፡ እሱም ማመንና የሚችሉትን ያህል ሁሉ ማግኘት ነው፡ በኢየሱስ እግር ሥር እንደተቀመጠችው እንደ ማርያም አድርገው ይይዙታል።

36 ማርታም ምሳውን ታዘጋጅ ነበር፡ ኢየሱስም አላት፡ "ይኸውልሽ፡ ማርታ፡ ስለ ሕይወት ነገር እጅግ ትጨነቂያለሽ፡ ማርያም ግን የተሻለውን ነገር መርጣለች፡" አያችሁ፡ የዘላለም ሕይወት ነገር።

37 አሁን፡ እንዳየናቸውም ይህን የተረዱት ብዙዎቹ ሰዎች... እንደ ዛሬው ዘመን ጽሑፎች አልነበሯቸውም፡ የዚያ ዘመን፡ ቴሌቪዥን ወይም ስልክ፡ ወይም ምንም ዓይነት ነገር አልነበራቸውም፡ ነገር ግን እርሱ በፋሲካ ላይ እንደሚገኝ በወሬ ደረጃ ተሰምቶ ነበር። ምክንያቱም ብዙዎቹ ሰዎች፡ መንፈሳዊ-አስተሳሰብ ያላቸው በመሆናቸው፡ የፋሲካው በግ እርሱ መሆኑን ያውቁ ነበር፡ ምክንያቱም ሊሆኑ ያሉትን ነገሮች ቀድሞ ነግሯቸው ነበርና።

38 ከዚያም፡ በእርግጥ፡ እርሱ በዚያ እንደሚገኝ እያወቁና፡ እንደዚያም ይወዱት ስለነበር፡ ይጠባበቁት ነበር። ከአንዱ በር ወደ ሌላው በር የሚገፋፋና የሚሻማ፡ በማንኛውም መንገድ፡ የሚጠባበቅ ሕዝብ ነበረ፡ ምክንያቱም ከነዚያ ሰዓታት በአንዱ እንደሚገለጥ ያውቁ ነበርና። ይጠባበቁም ነበር።

39 ሌሎች ደግሞ ከበር ወደ በር በሚሮጡት በእነዚህ ሰዎች ላይ ምን እንደተፈጠረ ያስቡ ነበር። "ትኩረት ሳቢው ነገር ምንድን ነው? "

40 ለማወቅም፡ **ወደዚህ**ና **ወደዚያ** ይመለከቱ ነበር። የሆነ ነገር እንደሚከሰት በመጠባበቅ፡ የሆነ ነገር የሚፈልጉ ይመስሉ ነበር።

41 ኦህ፡ ለጥቂት ደቂቃዎች ጥቅሴን ለወጥ አድርጌ፡ ዛሬም ያለው ነገር ይሄው መሆኑን ብነግራችሁ እንዴት ደስ ባለኝ። መምጣቱን በናፍቆት የሚጠባበቁት ወገኖች በታላቅ ጉጉትና ተስፋ ውስጥ ይገኛሉ። ጫናውን፡ ይሰማናልና። እያንዳንዱን እንቅስቃሴና ምልክት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እያመሳከሩ፡ በትጋትም ይመረምራሉ፡ ይከታተላሉም።

42 ስለ እርሱ የተነገሩትን እነዚያን የትንቢት ቃላት፡ እስከ ፍጻሜው ድረስ ሲያዩ፡ መጨረሻው እንደቀረበ ተገነዘቡ። በሰፍራው ለመገኘት በብርቱ ይመኙ ነበር፡ በንቃትም ይጠባበቁ ነበር። ከሕዝቡ መካከል፡ በቁጥር ጥቂት የሆኑት ከእርሱ ጋር ነበሩ። ሌሎቹ ግን ይቃወሙት ነበር፡ አብዛኞች፡ ይልቁንም ዘጠና በመቶ የሚሆነው ይቃወመው ነበር።

43 ዛሬም በሃይማኖተኛው ስብሰብ ውስጥ ያለው እውነት ይሄው ነው፡ ነገሩ ወደ ቃሉና ወደ ክርስቶስ ሲመጣ፡ የሚያምነው አንድ በመቶ ያህሉ ብቻ ነው። ቀሪው ሕዝብ ግን ምንም ቢደረግ፡ ግድ የለውም፡ በፌዝና በቀልድ ያልፉታል ወይም ያጣጥሉታል። ልክ ያው ነው። ጊዜ፡ ሁኔታዎች ብዙም አይለወጡም፡ ታሪክ ራሱን ይደግማል እንጂ።

44 እሺ፡ ይህም ትልቅ ውጥረትን እንዳስከተለ ደርሰንበታል። መሆንም ነበረበት። የግድ ማስከተል ነበረበት። እርሱ እዚያ ሲደርስ ምን ሊያደርግ እንደሚችል በጉጉት እያሰቡ፡ ይጠባበቁ ነበር። የሚያደርገውን ማንኛውንም ተአምር ለማየት በሰፍራው መገኘት ይፈልጉ ነበር። በጣም ይፈልጉት ነበር። ሊያዩት ይሹ ነበር። ያምኑት ነበርና። ሌሎቹ ግን እንደሚመጣ ሰምተው፡ ሊያፌዙበትና ሊሳለቁበት ነበር ወደዚያ የሄዱት። ከዚህ ሁሉ አስጨናቂ ተስፋና ጥበቃ በኋላ፡ እጅግ ልዩ በሆነ ዕለት፡ እጅግ ልዩ በሆነ ጊዜ፡ አብያተ ክርስቲያናት አንቀላፍተው፡ የሰዎቹ ትዕግሥት ተሟጦ፡ ሰፍራውም በሰው ተጨናንቆ ሳለ፡ ድንገት ያ ነገር ተከሰተ!

45 በደብረ ዘይት ተራራ አናት ላይ፡ አንዲት ትንሽ ነጭ አህያ ብቅ አለች፡ ከተራራው ቁልቁል እየወረደች፡ ቁጥራቸው የበዛ ወገኖችም በታላቅ ጩኸት እየተከተሏት፡ የዘንባባ ቅጠሎችን ከዛፎች ላይ እየቆረጡ፡ ልብሳቸውንም በመንገድ ላይ እያነጠፉ፡ እንዲህ እያሉ ይጮኹ ነበር፡ “በጌታ ስም ለሚመጣው ለዳዊት ልጅ ሆሳዕና!” ይህቺ... ይህቺ ትንሽ አህያ፡ ጋላቢዋ የዚያች ዘመን በእግዚአብሔር የተቀባው መሲሕ እንጂ ሌላ ማንም አልነበረም።

46 ይህ ከሆነ፡ ታዲያ፡ እግዚአብሔር ምን እያደረገ ነበር? ኮረብታው ላይ የነበረው ትኩረት ሳቢው ነገር ምንድን ነው? እግዚአብሔር ታሪክን እየሰራ፡ ትንቢቱንም እየፈጸመ ነው። ይህም ሁልጊዜ ሰህበትን ይፈጥራል። ተቺዎችን ሁሉ፡ ጥንብ አንሣዎቹን (የጠዋቱን መልእክት አሰቡ)፡ እንዲሁም ንሰሮችን በአንድነት ይሰባል። አያችሁ? ምን እየተካሄደ እንዳለ ለማየት በአንድነት ተሰበሰቡ። አንዳንዱ የማወቅ ጉጉት፡ አንዳንዱ እንከን ለመፈለግ፡ ሌላውም ለመተቸት ይመጣል። ዛሬ ጠዋት እንዳልነው፥ በዚያ ሁሉ ዓይነት ሰው ተሰብስቧል፡ አማኞች፡ አስመሣይ-አማኞች፡ የማያምኑም። ተራራው ላይ ያለው ምንድን ነው? ትንቢቱ እየተፈጸመ ነው። አሁን ምን እንደተከሰተ እንመለከታለን።

47 አሁን፡ በዘካርያስ መጽሐፍ፡ ምዕራፍ 9 ከቁጥር 9 ላይ። ከነቢያት አንዱ የሆነው ዘካርያስ በመንፈስ ሆኖ እንዲህ ሲል ተናገረ።

> **“የጽዮንም** ቈነጃጅት **ሆይ፡ እጅግ ደስ ይበላችሁ፡ እናንተ የኢየሩሳሌም** ቈነጃጅት፡ **እልል በሉ፥ እነሆ፡ ንጉሣችሁ ወደ እናንተ ይመጣል፥ እርሱ ጻድቅና፡... የሚያድንም ነው፥ ትሑትም ሆኖ፡ በአህያም በአህያይቱ ግልገል፡** በውርጫይቱ **ላይ፡ ተቀምጦ ወደ እናንተ ይመጣል።**

48 ታዲያ፡ እነዚያ ጻፎች ምን ሆነው ነበር? እነዚያ ካህናትስ ምን ነካቸው? የእነዚያ ሃይማኖተኛ ሰዎች ችግር ምን ነበር? ይህ ከመፈጸሙ ከአራት መቶ ሰማንያ-ሰባት ዓመታት በፊት፡ በተረጋገጠ ነብይ ተጻፈ፡ በጽሑፍ ሰፍሮም መጽሐፍ ቅዱስ፡ የብሉይ ኪዳን ጥቅልሎች ተብሎ ተጠርቷል። ያ ትንቢት እየተፈጸመ እንደሆነ ለምን ማየት አቃታቸው? ዛሬም ማየት ለተሳናቸው በተመሳሳይ ምክንያት ነው። ትምህርቱን (በትውፊቶች) ለውጠው፡ የእግዚአብሔርን ቃል በሕዝቡ መካከል ከንቱ አደረጉት በሰው ልጆች ትውፊቶች ትምህርት ተኩት።

49 እነዚያ ጻፎች፡ ሰባኪዎች፡ አገልጋዮች፡ መንፈሳዊ ሰው (ነን-ባዮች)፡ የተቀበሉት ሁሉ፡ መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ ቢያነቡ ኖሮ፡ ምን እየተካሄደ እንዳለ ግራ አይገባቸውም ነበር፡ ነገሩ ምን እንደሆነ በግልጽ ያውቁት ነበር። ይኸው እግዚአብሔር ቃሉን እየፈጸመ ነው!

50 ታሪክ እየተመዘገበ፡ ትንቢት እየተፈጸመ ነበር። ለዓለም ድነት ይመጣ ነበር፡ ነቢያት ሁሉ በጉጉት የጠበቁት ያ ታላቅ ዕለት መጣ። በመቃብር ውስጥ ያሉት ሁሉ ያንን ዕለት ይጠባበቁ ነበር (አቤት፡ እስኪ አስቡት)፡ የሞቱት ሁሉ፡ በሰማዕታትና በነቢያት ደም የጸደቁት በሙሉ ያንን ቀን ይጠባበቁ ነበር።

51 በዚህም፡ ምክንያት በታላቅ ድምፅ እንዲህ ሲል ጮኸ፡ “ኢየሩሳሌም፡ ኢየሩሳሌም ሆይ፡ ወደ አንቺ የሚላኩትን ነቢያትን የምትወግሪ፡ ጻድቃኑንም የምትገዪ፡ ዶሮ ጫጩቶቿን በክንፎችዋ ሥር እንደምትሰበስብ፡ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድኩ፡ አንቺ ግን አልወደድሽም። አሁን ግን ሰዓትሽ ደርሷል።”

52 በመቃብር ውስጥ የነበሩት በሙሉ፡ አብርሃም፡ ይስሐቅ፡ ያዕቆብ፡ ነቢያቱም ሁሉ፡ ይህችን ሰዓት ይጠባበቁ ነበር።

53 ቤተ ክርስቲያን ግን ለዚህ ነገር ዕውር ነበረች። “ይህ ሁሉ ረብሻ የሚፈጥረው ማን ነው? ይህ ሰውዬ ማነው?” አንድ ጊዜ እንዲህ አሉ፡ “ይህ የጸራቢው ልጅ አይደለምን? እርሱን እኮ እናውቀዋለን። ይህንን ጥበብ ከየት አገኘው? እንዴት፡ እኛ ከማናቸውም ትምህርት ቤቶቻችን ጋር ሲገናኝ አላየነውም። የተማረበትንም መጽሐፍ አናውቅም። ለመሆኑ ማን ነው?”

54 እርሱ ለነቢያት ትንቢት ሁሉ የተሰጠ መልስ ነበረ። እነሆ፡ በአህያ ውርንጫ ላይ ተቀምጦ መጣ። እንዴት ያለ ታላቅ ስህበት ነው! እግዚአብሔር የገባውን የኪዳን ቃል እየፈጸመ ነበር፡ ከአራት ሺህ ዓመታት ጀምሮ ሲጠበቅ የነበረው ሰዓት ደረሰ። በዘፍጥረት፡ ምዕራፍ 3 ቁጥር 15 ላይ፡ እግዚአብሔር እንዲህ ሲል አስቀድሞ ተናግሮ ነበር፡ “የሴቲቱ ዘር የእባቡን ራስ ይቀጠቅጣል፡ ነገር ግን እባቡ ተረከዟን ይቀጠቅጣል፡” በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለዚህ ሰው መምጣት የተነገረው ትንቢት ይኸው ነበር።

55 በቅርቡም በመካከላቸው፡ እውነተኛ መሆኑን የተረጋገጠ ነብይ ተነሥቶ ነበር፡ ዘካርያስ፡ እርሱም፡ እንዲህ አለ፡ “እናንተ የኢየሩሳሌም ሴቶች ልጆች የጽዮንም ሴቶች ልጆች ሆይ፡ ደስ ይበላችሁ፡ እልል በሉ፡ ጩኹም፡ እነሆ ንጉሳችሁ ትሁት ሆኖ፡ በአህያ ውርንጫ ላይ ተቀምጦ፡ ወደ እናንተ ይመጣል።”

56 ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡ ዕለት በዕለት የሚያነቡት እነዚያ ሰዎች፡ እየጋለበ ሲመጣ ተመልክተው፡ እንዲህ አሉ፡ “ይህ ማን ነው?” አያችሁ? ምን እንደሆነ ለሚያውቁ ለእነዚያ ሰዎች እግዚአብሔር ቃሉን እየፈጸመ ነበር፡ ነገር ግን አላወቁትም።

57 እግዚአብሔር ቃሉን ሲፈጽም፡ ሁልጊዜም መሰህብን ይፈጥራል፡ ሁልጊዜም እንዲሁ ነው። ያልተለመደ ነገር ስለሆነ፡ መሰህብን ይፈጥራል። የዚህ ዘመን ዘመናዊ አካሄድ፡ በእሱ ስለማያምን፡ በዘመናዊው አካሄድ ቃሉን ሲፈጽም እጅግ ያልተለመደ ይሆንባቸዋል። የራሳቸው መንገድ አላቸውና።

58 አሁን፡ እንመልከት፥ እግዚአብሔር ትንቢቱን እንዴት እንደፈጸመ ለጥቂት ደቂቃዎች ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እንመለስና፡ ሌሎች ያልተለመዱ ሁኔታዎችን፡ እንመልከት። እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር ከተናገረ፡ ያደርገዋል። ሰማይና ምድር ያልፋሉ፡ ያ ቃል ግን ከቶ አያልፍም። ስለዚህ ብዙውን ጊዜ ትዕይንትን፡ ያልተለመደ ትዕይንትን ይፈጥራል።

59 ያምኑታል ለሚባሉ ሰዎች የእግዚአብሔር ቃል ምን ያህል የሚያሰቅ እንደሚሆንባቸው አስተውሉ፡ እናም እጅግ ያልተለመደ ስለሚሆንባቸው እንዲህ ብለው ይጮኻሉ፡ “ለመሆኑ፡ ይህ ምንድን ነው? ይህንን ነገር ከየት አመጣኸው? ይህ ማን ነው? ይህ ምንድን ነው?”

ሆኖም፡ “በጌታ ስም ለሚመጣው ንጉሥ ሆሳዕና፡” እያሉ መጮኽ በተገባቸው ነበር! ነገር ግን ይህንን የሚያደርጉት ጥቂት ቡድኖች ብቻ ነበሩ፡ ጥቂት ቡድኖች ብቻ።

ለአገሪቱ ሊሆን ከሚችለው ከሁሉ የላቀው ነገር ላይ፡ አራት ሺህ ዓመታት ሙሉ ትንቢት ሲነገርለት፡ የሙታን ተስፋ ሁሉ በእሱ ላይ አርፎ፡ የወደፊቱ ጊዜ ሁሉ በእሱ ላይ ተመሰርቶ ሳለ፥ እንዲሁም እኛ አማኞች ነን የሚሉቱ፡ ሃይማኖተኞች፡ እንዲህ እያሉ ይጮኹ ነበር፡ “ይህ ማን ነው? ይህስ መሰህብ ምንድን ነው?” ያልተለመደ ነገር! አሁንም ያው ነው፡ ምንም አይለወጥም፡ ያልተለመደ ነገር ነው።

60 እንዳልኩት፡ እስኪ አንዳንድ ያልተለመዱ ነገሮችን እንመልከት። ፍርድ ዓለምን መትቶ በውሃ ከማጥፋቱ በፊት የነበረው መሰህብ ምን ነበረ? አንድ ሰው፡ ዕድሜው ወደ መቶ ሃያ ዓመት ገደማ የሆነ፡ ምንም የሚያንሳፍፈው ውሃ በሌለበት ሰፍራ መርከብ ይሠራ ነበር። ለዓመታት፡ በዚያ በር ላይ ቆሞ፡ ውስጡን እየገነባ፡ በውስጥና፡ በውጭ ቅጥራኑን ሲለቀልቅ፡ ታላቁ የሳይንስ ዘመን እያለ፡ “ዓለም በውሃ ልትዋጥ ነው፡” ይል ነበር።

61 “እዚያ ኮረብታ ላይ የሚሰማው የሞደሻ ድምጽ ምንድን ነው?” “እንዴ፡ ኖኅ የሚባለው አንድ ሽማግሌ ነው፡ እዚያ ላይ ያለ፡ ያረጀ አክራሪ ነው። ሽማግሌው በፀሐይ ውስጥ በጣም ረጅም ጊዜ ቆሟል። ፀሐይ መትቶታል። አእምሮውን ስቷል። እርሱ ‘መርከብ’ ነው የሚለውን ነገር እየሠራ ነው፡ ምንም ውሃ ከሌለበት ከላይ ውሃ እንደሚመጣና፡ ሰዎችን ሁሉ እንደሚያንሳፍፍ ይናገራል፥ ደግሞም መልእክቱን የማይሰማውና፡ ወደዚያ መርከብ የማይገባው ሁሉ፡ ይሰጥማል ይላል። እንዲህ ዓይነት ነገር ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?” እጅግ ያልተለመደ ሰህበት ነበር!

62 ሰዎቹ በደንብ መሳቅ ሲፈለጉ፡ በመርከቡ በር ፊት ቆመው ይስቁ እንደነበር አሰባለሁ። “እንዴ፡ ከአንድ መቶ ዓመት በፊት ዝናብ ይዘንባል ትለን ነበር! አያቴም በዚያ ዘመን ዝናብ ይዘንባል ስትል ይሰማህ እንደነበረ ነግሮኛል፡ አንተ ግን አሁንም ያረጀውን የእንጨት ቁራጭ ትደበድባለህ። ለምን ወደ አእምሮህ አትመለሰም?”

63 እግዚአብሔር ግን የገባውን ቃል ሊያረጋግጥና ነቢዩ የተናገረውን ትንቢት ሊፈጽም ዝግጅት ላይ ነበር። በጣም ያልተለመደ! ሌሎች እየተሳለቁ ሳሉ፡ እግዚአብሔር ለኖህ የገባውን ቃል ይፈጽም ነበር። እግዚአብሔር ቃሉን፡ እስከ ዛሬ ድረስ እንደሚጠብቅ ለሌሎች ለማሳየት፡ ታሪክን ሊመዘግብ ዝግጁ እየሆነ

ነበር! ምን ያህል እውነት ባይመስልና፡ ምክንያታዊ ባይሆንም እንኳ፡ እርሱ አሁንም ቃሉን ይጠብቃል። ያንን መርከብ በሚደበድበው፡ በዚያ የዕድሜ ባለጸጋ ሰው በኩል፡ ዛሬ ምሽት እዚህ አሜሪካ ላላችሁና በመላው ዓለም ላሉት ሰዎች ምሳሌ ያደርገው ነበር። ሳይንስ ምንም ቢናገር፡ ምንም ቢናገር፡ **ይህ፡ ያ፡** ወይም **ሌላ** ቢናገር፡ አሁንም ቃሉን ይጠብቃል። እሱ ታሪክ እያደረገ ነበር።

64 በአንድ ወቅት በምድረ በዳ ውስጥ፥ አንድ ያልተለመደ ነገር ሲከሰት መሰህቡ ምን ነበር፡ በቁጥቋጦው ላይ እሳት ይነድ ነበር። የኮበለለውም ነቢይ በምድረ በዳ ውስጥ ቆሞ ነበር። ምንም ድምፅ አልሰማም፡ ምንም ዓይነት ድምፅ አልነበረም፡ ነገር ግን ተመልክቶ በተራራው እናት ላይ ያልተለመደ ነገር አየ። እግዚአብሔር ትኩረቱን ለመሳብ ይሞክር ነበር። ዛሬም ሁኔታው ያው ነው!

65 እግዚአብሔር በነቢዩ በአብርሃም በኩል የተናገረውን ቃል፡ ለመፈጸም እየተዘጋጀ ነበር፡ "ዘርህ በባዕድ አገር አራት መቶ ዓመታት ይቀመጣል። በብርቱ እጅ አወጣቸዋለሁ።"

66 ለሚያምኑት ሁሉ ደኅንነታቸው የሚጠበቅበትን መርከብ እንደሚያዘጋጅ ሁሉ፡ ለዚያም ሥራ አንድ ሰውን እያዘጋጀ ነበር። እግዚአብሔር ቁጥቋጦውን በእሳት አቀጣጠለው፡ እረኛው፡ ሙሴም፡ "ይህ ድንቅ ነገር ምን እንደሆነ ለማየት ጠጋ ልበል፡" አለ። ሙሴንም ወደ ቁጥቋጦው እንዲቀርብ ባደረገው ጊዜ፡ አናገረው።

67 በኋላም ያ እረኛ በጲላጦስ አዳራሽ በትር በጣለ ጊዜ፡ ወደ እባብ ስትለወጥ መሰህቡ ምን ነበር? እግዚአብሔር ለሙሴ የገባውን ቃል መፈጸሙ ነበር። በቀይ ባሕር ላይስ፡ የፈርዖን ፈረሶች በደነገጡ ጊዜ፡ ከሰማይ የመጣው ነፋስ ባሕሩን ከቀኝ ወደ ግራ ሲከፍለው ባዩ ጊዜ፥ በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚጓዙት፡ እነዚያ ምስኪን ባሮች፡ በደረቅ ምድር ሲሻገሩ መሰህቡ ምን ነበረ? ምን ነበር? እግዚአብሔር ቃሉን መጠበቁ ነበር። የሞተው ነገር ፈቀቅ አለ፡ ሕያዋኑ ወገኖች ተሻገሩ፥ በመንፈስ የሞቱት ህዝብ ግን ሊመስሏቸው ሞክረው፡ ሰጠሙ። እግዚአብሔር ትንቢቱን እየፈጸመና ታሪክን እየሠራ ነበር። በሙት ባሕር ላይ የነበረው መሰህብ ይኸው ነበር።

68 ከዚያ በኋላ በሁለተኛው ቀን፡ በሲና ተራራ ላይ፡ ሕዝቡ ሁሉ ወደ ሚስቶቻቸው እንዳይቀርቡ ሲታዘዙ፡ ልብሳቸውን እንዲያጥቡና ራሳቸውን እንዲቀድሱ ሲጠየቁ፡ ሙሴ የተባለው ሰው እግዚአብሔርን በእሳት ዓምድ ውስጥ እንዳገኘው በተናገረበት ተራራ ዙሪያ ሲሰበሰቡ የነበረው መሰህብ ምን ነበር? እግዚአብሔርም ለሙሴ እንዲህ ብሎት ነበር፡ "በሕዝቡ መካከል እወርዳለሁ። የነገርኩህን ቃልና፡ እኔ ማን እንደሆንኩ አጸናለሁ። እኔ ያ አምላክ መሆኔን አሳያቸዋለሁ።" መሰህቡ ያ ነበር፡ እግዚአብሔር ቃሉን ሲፈጽም።

69 በአንድ ወቅት በታሪክ ውስጥ፡ አንድ ሕዝብ እግዚአብሔርን በረሳበት፡ ሕዝቡ ሥርዓታዊና ግዴለሽ በሆነበት፡ ካህናቱ ሁሉ ከዘመናዊው ዝንባሌ ጋር በሄዱበት፡ ነቢያቱም እንደ ካህናቱ ፈቃድ ትንቢት በተናገሩበት ወቅት የነበረው መሰህብ ምን ነበር? በዚያን ቀንም፡ እንደተለመደው፡ አክራሪ ነው ብለው የሚያስቡት አንድ ሰው አገኙ። እርሱም ሴቶች መዋቢያ ቀለም ስለመቀባታቸውና፡ ስለ ሁሉም ነገር ይናገራቸው ነበር፡ እርሱ የሆነ ለየት ያለ

ሰው ነበረ። እናም ይህ አዛውንት ወርዶ ለንጉሡ እንዲህ አለው፡ “ከእፌ ቃል በቀር… ጠል እንኳን አይወርድም።”

70 በመሁኑም፡ እርሱ ራሱን ደብቆ ከዚያ እንደኮበለለና፡ በምድረ በዳ ውስጥ የሆነ ቦታ ተሸሽጎ እንደነበረ፡ ደርሰንበታል። ሰዎቹ ምናልባት በራብ ሞቶ ወይም ጠፍቶ ይሆናል ብለው አሰበው ነበር፥ ነገር ግን በጥሩ ሁኔታ ይመገብና፡ ውሃም፡ ያገኝ ነበር። እነሆም፡ እርሱ ወርዶ እንዲህ አለ፡ “**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** የሚል ቃል እንዳለኝ ታያላችሁን? አሁንም፡ ይህ ካላሳመናችሁ፡ ወደ ተራራው እናት እንውጣና እውነተኛው አምላክ ማን እንደሆነ እናረጋግጥ፡” ከጌታ ዘንድ ሌላ ራእይ አይቶ ነበርና።

71 እርሱም፡ “መሠዊያን እናንተ ምረጡ፡ ሥሩትም፡ እና—እና በሬ መርጣችሁ እረዱ። እኔም የጌታን መሠዊያ እሠራለሁ፡ በሬንም በላዩ ላይ እኖራለሁ። ሁለታችንም መሥዋዕት እናቀርባለን፡ እውነተኛውም አምላክ በእሳት ይመልስ።” ጌታ ካልነገረው በቀር ይህንን በጭራሽ አያደርገውም ነበር፥ በኋላም እንዲህ ብሏል፡ “ጌታ ሆይ፡ ይህንን ሁሉ… ይህንን ሁሉ ያደረግሁት፡ በአንተ ትዕዛዝ ነው።”

72 ታዲያ መሰህቡ ምን ነበር? አራት መቶ ካህናት በኮረብታው ላይ ቆመዋል፡ ንጉሡም በሰረገላው ላይ ሆኖ፡ ከሰራዊቱና ከጠባቂዎቹ ጋር በዙሪያው ቆሟል። ይህም ያረጀ፡ ጸጉራም፡ ፊቱ-በጠጉር-የተሸፈነ፡ ራሰ በራ የሆነና፡ ጸጉሩ በፊቱ ላይ የተንጠለጠለ፡ የበግ ቆዳ የለበሰ ሰውነቱ ሁሉ በጸጉር የተሸፈነ ሰው፡ በትር በእጁ፡ በሌላኛው እጁም፡ ማሰሮ ዘይት ይዞ ቆሟል፥ ከሦስት ዓመት ተኩል በፊት፡ “ከእፌ ቃል ካልወጣ በቀር፡ ጠል እንኳ አይወርድም፡” ብሎ የተናገረው እርሱ ነው፡ እነርሱ ሰለሚናገሩላቸው፡ እንደ ብርሃናዊ አክሊሎችና ጥላዎች ባሉ ነገሮች፡ የእግዚአብሔርን ሰፍራ የወሰደ ነው። “እነሆም ያ አክራሪ ሽማግሌ እዚያ ኮረብታ ላይ ቆሞ፡ እነዚህን ሰዎች ሁሉ ወደዚያ አሰመጣቸው። ታዲያ መሰህቡ ምን ነበር? እግዚአብሔር የነቢዩን እውነተኛነት ሊያጸና ዝግጁ ሲሆን ነው። እግዚአብሔር ትንቢቱን ሲፈጽም ነው። እግዚአብሔር ቃሉን እየፈጸመና፡ ታሪክን እየሠራ ነበር።

73 ከዚያ ከጥቂት መቶ ዓመታት በኋላ፡ በዚያው መንፈስ የተቀባ አንድ ሰው ነበረ፡ እርሱም ከምድረ በዳ ወጣ፡ አባቱ የድርጅት ሰው፥ የአንድ ሥርዓት ካህን ቢሆንም እንኳ፡ ከማንኛውም ድርጅት ጋር ግኑኝነት አልነበረውም። ነገር ግን እርሱ የበግ ቆዳ ለብሶ፡ ፊቱ በጠጉር ተሸፍኖ፡ ከምድረ በዳ ወጣ። ጠጉሩ ሽበት ሳይሆን፡ ጥቁር ነበር። የዚህ ሰው ኢየሩሳሌምንና ይሁዳን ሁሉ የሳበው መሰህብ ምንድን ነው? አንዳንዶቹ ወጥተው እንዲህ ይሉ ነበር፡ “በዚያ በኩል አንድ አውሬ ሰው አለ። ሰዎችን በውሃ ውስጥ ሊያሰጥም ይሞክራል። እንዲህ ዓይነት ነገር ማን ሰምቶ ያውቃል? ”

74 ሌሎች ደግሞ ለማወቅ ይጓጉ ነበር፡ “ይህ መሲሕ መሆን አለበት፡” ይሉ ነበር። ከመካከላቸው አንዱ፡ “ከነቢያት አንዱ ሊሆን ይችላል” ብሏል። ምን እንደሚያሰቡ አያውቁም ነበር። ነገር ግን ምን ነበረ? እግዚአብሔር የኢሳይያስ 40ን ትንቢት ሲፈጽም ነበር፡ ይህም እርሱ፡ “እነሆ… ” እንዲህ ይሆናል እያለ በመጨረሻው ዘመን ምን እንደሚያደርግ፡ አገልጋዩን እንዴት እንደሚልክና ምን እንደሚያደርግ የተናገረለትን ነው።

75 በመሁኑም፡ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ፡ ያ ሰው ስለ መልእክቱ እጅግ እርግጠኛ እንደነበረ ደርሰንበታል፡ እንዲህም እስኪል ድረስ፡ “እኔ የእርሱ ጫማ ልሸከም የማይገባኝ፡ እነሆ አንዱ በመካከላችሁ ቆሟል። እኔ በውሃ እንዳጠመቅሁ፡ እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል።”

76 አንድ ቀን፡ የሠላሳ ዓመት ዕድሜ ገደማ ያለው፡ ተራ የሆነ ወጣት ሰው፡ ወረደና ተጠመቀ። ይህ ሰው በመጣ ጊዜም፡ በነቢዩ ዘንድ ለየት ያለ መሰህብ ስለነበር፡ በዚያ ቀን ነቢዩ እንግዳ ድርጊት አደረገ። ጉባኤውም የዚያን ነቢይ ድርጊት ከመመልከት ወደ ኋላ ማለት አልቻለም።

77 በወንዙ ማዶ ካሉት ካህናት ጋር ይከራከር በነበረበት ጊዜ፡ እነርሱም እንዲህ አሉ፡ “ይህንን መሠዊያ የሠራው እግዚአብሔር ነው። ይህንን እንድናደርግ እግዚአብሔር አዘዘን። ሙሴ ነቢይ ነው። በሙሴ እናምናለን። መሥዋዕቱም ከቶ አይጠፋም።”

78 ዮሐንስ ሲመልስላቸውና፡ እንዲህ ሲል እሰማዋለሁ፡ “በመጽሐፍ ቅዱስ ነቢዩ ዳንኤል ስለ ዘወትር መሰዋዕት እንዲህ ሲል የተናገረውን አልሰማችሁምን፡ ‘የዘወትር መሥዋዕት ይሻራል’? ያም ሰዓት ደርሷል! ኢሳይያስ በምዕራፍ 40 ላይ እንዲህ ሲል የተናገረውንስ አላነበባችሁም፡ ‘የጌታን መንገድ አዘጋጁ እያለ፡ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ’? እነዚህ ስለ እኔ የተነገሩ ሁለት ትንቢቶች ናቸው። ሌላው ነገር ደግሞ፡ ከአራት መቶ ዓመታት በፊት፡ ነቢያችን ሚልክያስ፡ ምዕራፍ 3 ላይ ሲናገር፡ ‘እነሆ፡ መንገዱን ያዘጋጅ ዘንድ፡ መልእክተኛዬን በፊቴ እልካለሁ’ ባለ ጊዜስ? ይህ ትንቢት እንደሚፈጸም አታውቁምን? ” ትንቢት ይፈጸም ነበር!

79 ወዲያውኑም ነቢዩም ዘወር አለና እንዲህ አለ፡ “እነሆ፡ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ!” አሁንም መሰህቡ ምንድን ነው? ከነቢዩ ወደ ትንቢቱ ተለውጧል።

80 አሁን የሚሆነውን ልብ በሉ። እነሆም፡ በማንም ዘንድ የማይታወቅ፡ የጸራቢ ልጅ የሆነ፡ ተራ ሰው በውኃው ላይ እየተራመደ መጣ። ታላቁ ነቢይ፡ ዮሐንስም፡ አለው፡ “እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል። አንተ ለምን ወደ እኔ ትመጣለህ? ”

81 እርሱም መልሶ፡ “አሁንስ ፍቀድልኝ። ሆኖም፡ እንደ ነቢይና እንደ ቃል፡ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና።”

82 ስለዚህ መሥዋዕቱ ከመቅረቡ በፊት መታጠብ እንዳለበት አስተዋለ፡ አጠመቀውም።

83 አሁን ከውኃው በወጣ ጊዜ ሌላ መሰህብ ተከሰተ። የገዛ ዘመኑን እና ጊዜውን በአዋጅ ለመናገር እጅግ ታማኝ የነበረው ይህ ነቢይ፡ ቀና ብሎ ሰማያትም ሲከፈቱ ተመለከተ። የእግዚአብሔርን መንፈስ፡ እንደ ርግብ ሲወርድበት፡ በእርሱ ላይ ሲያርፍበት አይቷል፡ ድምጽም፡ “በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው” አለ። እግዚአብሔር የነቢዩን መልእክት ያጸና ነበር፡ በዮርዳኖስ ወንዝ ዘንድ መሰህብ ሆኖ የሳበው ነገር ያ ነበር።

84 ከጥቂት ጊዜ በፊት አንድ ወንድም “በሩቅ ኮረብታው ላይ ያረጀው ሻካራ መስቀል ቆሟል፡” እያለ ዘምሮታል፡ ወይም ሊዘምር ተዘጋጅቶ ነበር። የቀራንዮው ተራራ መሰህብ ምንድን ነው? የሃይማኖቱ ዓለም እንደኰነነው፡

የሮምም መንግሥት ለሞት እንደፈረደበት ስንመለከት። እርሱም ይኸው በሁለት ወንበዴዎች መካከል ተሰቅሏል፡ መጠጥ ተጠምቶ፡ ደሙም ከሰውነቱ ላይ እየፈሰሰ። በዚያ ተሰቅሎ፡ እንዲህ እያለ ጮኸ፡ "አምላኬ፡ አምላኬ፡ ለምን ተውኸኝ?" የሃይማኖት ሰዎቹም በዚያ ቆመው፡ ይመለከቱት ነበር፡ የብሉይ ኪዳን ትንቢት በዚያን ጊዜ በቀራንዮ ላይ እየተፈጸመ እንደነበረ ፈጽሞ አላስተዋሉም ነበር።

85 ዳዊት ራሱ ሲጽፍ፡ ተ... እንደ ሁሉም ነቢያት በመንፈስ ተሞልቶ ተንቀሳቀሰ፡ ስለ ራሱ የሚናገርም ይመስል ነበር። ዳዊት፡ በ22ኛው መዝሙር ላይ፡ "አምላኬ፡ አምላኬ፡ ለምን ተውኸኝ? አጥንቶቼ ሁሉ ይመለከቱኛል። እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩት።" ዳዊት፡ ስለ ራሱ እንደሚናገር ይመስል ተናገረ። እርሱ ግን ዳዊት አልነበረም፡ በዳዊት ውስጥ የነበረው ክርስቶስ ነበር እንጂ።

86 የተለያዩ ነቢያት የተናገሩት፡ ያ ትንቢት ሁሉ፡ በቀራንዮ ተራራ ላይ እየተፈጸመ ነበር። የቀራንዮው ተራራ መሰህብ ምንድን ነው? እግዚአብሔር ቃሉን ሲፈጽም።

87 ሌላው መሰህብ ደግሞ፡ በተራራ ላይ በጴንጤቆስጤ ቀን ነበር፡ ሁሉም በሃይማኖታዊ በዓል ላይ በነበሩበት ወቅት፡ አክራሪዎችን ሁሉ ያሰወገዱ መሰሏቸው ነበር። ለአሥር ቀናት ያህል ከእነርሱ ምንም አልሰሙም ነበርና። ድንገትም፡ እንደ ቀፎ ንብ፡ ከህንጻው ላይ ተነሰተው፡ እየጮኹና ድምፅ እያሰሙ፡ ወደ ጎዳናዎች ፈሰሱ።

88 "ይህ ምንድን ነው? ይህ ምን ማለት ነው? ሁሉም ሰክረው ይሆን?"

89 ይኸውላችሁ! እንደ ነቢይ ሥርዓትም፡ አንድ ነቢይ ከመካከላቸው ተነሣና፡ እንዲህም አለ፡ "እናንተ የእስራኤል ሰዎች ሆይ፡ በይሁዳም የምትኖሩ፡ በኢየሩሳሌም የምትኖሩ ሁሉ፡ ይህ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን፡ ቃሎቼንም አድምጡ። እነዚህ እናንተ እንደመሰላችሁ የሰከሩ አይደሉም። ነገር ግን ይህ በነቢዩ በኢዩኤል፡ ከጌታ ዘንድ የተነገረው፡ 'በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፡ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ እፈሳለሁ።'" መሰህቡ ያ ነበር።

90 የሃይማኖት ሰዎቹ፡ የሕይወትን ራስ ከሰቀሉ፡ እና ሁሉንም ካደረጉ በኋላም፡ የመንፈስ ቅዱስን የመምጣት ተሰፋ አሁንም አላስተዋሉም ነበር። መሰህቡ፡ "ይህ ማን ነው? ትርጉሙስ ምንድን ነው? እነዚህ ሰዎች ምን ሆነዋል?"

91 ኦህ፡ ማይ! ዛሬም ያው ነው። ወደዚህ ዘመን ለመምጣት ብዙ ነገሮች እንዘላለን። ዛሬም ተመሳሳይ ነገር ነው። ተመሳሳይ ነገር እየሆነ ነው። ተመሳሳይ ጥያቄ ተጠይቋልና፥ "ይህ ሁሉ ጫጫታ ምንድን ነው?" በመንገዱ ወደ ላይና ወደ ታች ተመልከቱ፡ ከሚሺጋን እስከ ፍሎሪዳ፡ ከሜይን እስከ ካሊፎርኒያ የሚተላለፉ መኪኖች። ዛሬ ጠዋት በመኪና ሰወጣ፡ ማለቴ ከቀትር በኋላ፡ በመንገድ ላይ ስንጓዝ፡ ባለቤቴና እኔ የመኪና ታርጋዎችን እንመለከት ነበር። ይህን ጽሑፍ ያሰብኩት በዚያን ጊዜ ነው።

"ይህ ምን ማለት ነው?"

92 "ሰጋ ባለበት፡ በዚያ ንሰሮች ይሰበሰባሉ፡" እንደተባለው።

93 ባለቤቴን እንዲህ አልኳት፡ "የኔ ማር፡ በምድር ላይ ለእኔ ውድ የሆነው ነገር ሁሉ፡ ደህና-ሰንብት ብዬ እግዚአብሔር እንዳደርገው የተናገረውን

ነገር ለመጀመር፡ ወደ መሰክ የወጣሁበትን ያቺን የመጨረሻዋ ሌሊት ታስታውሻለሽ? ያንን መዝሙር ዘምረሽ ነበር።"

ኦህ፡ ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ፡
ከሩቅ አገር ይመጣሉ፡
ከንጉሣችን ጋር ለመብላት፡ እንደ እንግዳው ለመመገብ፥
እነዚህ ተጓዦች ምንኛ ብጹአን ናቸው!
የተቀደሰ ፊቱን የሚያዩ
በመለኮታዊ ፍቅር የበሩ፥
የጸጋው ተካፋዮች ብፁዓን ናቸው፡
በዘውዱ ውስጥ እንደ እንቁዎች ያበራሉ።

94 መሰህቡም ይሄው ነው። አስቀድመው ለተወሰኑ ለእግዚአብሔር ዘር ይህን ከመከተል ውጪ ሌላ ምንም ማድረግ ለማይችሉ፡ ለእኛ ከሕይወት የበለጠ ትርጉም አለው። ሕይወታችንን ውሰዱ፡ ነገር ግን ያንን አትወሰዱም። መሰህቡ ምንድነው? እግዚአብሔር፡ እንደተለመደው፡ ቃሉን መፈጸሙ ነው። እንደገና የዘካርያስን፡ የነቢዩን የዘካርያስን ቃል እየፈጸመ ነው።

95 ከጥቂት ጊዜ በፊት ያነበብኩት 9 ኛው ቁጥር ላይ፡ ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደሱ ሲገባ፡ እየጋለበ... ወይም ወደ ኢየሩሳሌም፡ በትንሿ ነጭ አህያ ላይ፡ ተቀምጦ እየጋለበ ሲገባ፡ ዘካርያስ እንዲህ ያለው ትንቢት ተፈጸመ። ይኸውም፡ "እናንተ የጽዮን ሴቶች ልጆች ሆይ፡ እጅግ ደስ ይበላችሁ። እናንተ የኢየሩሳሌም ሴቶች ልጆች ሆይ፡ እልል በሉ። እነሆ፡ ንጉሣችሁ ወደ እናንተ ይመጣል፥ እርሱ ጻድቅ፡ አዳኝም ነው፥ ትሑት ሆኖ፡ በአህያይቱና፡ በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ይመጣል።" በኢየሩሳሌም፡ በሃይማኖታዊው ጠቅላይ መሥሪያ ቤት የነበረው መሰህብም ይኸው ነበር።

96 አሁን የመጨረሻው-ዘመን ክስተት እንመለከታለን! በዘካርያስ መጽሐፍ ውስጥ፡ ጥቂት ገጾችን ገለጥ አድርገን፡ ሰለ እርሱ የተናገረውን እንይ። እንግዲህ ወደ ኋለኛው ቀናት ክፍል እናዙረው። ያኛው የመካከለኛው ዘመን ነበር፥ አሁን ግን ወደ ኋለኛው ቀናት እንግለጥ። ከዘካርያስ ምዕራፍ፡ አሥራ አራት ገልጠን፡ ከቁጥር አራት እንጀምር። አድምጡም! ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተወሰነውን ክፍል፡ ከቁጥር 4 እስከ 9 ያሉትን፡ ወደ ዘጠኝ የሚጠጉ ጥቅሶች እናነባለን። በትኩረት አድምጡ። ይህም ሰለ እርሱ መምጣት፡ ሰለ ኋለኛው ቀናት የተነገረ ትንቢት ነው። አሁንም በትኩረት አድምጡ። ይህም **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡ ዘካርያስ 14። ዘካርያስ ምዕራፍ 9፡ ምን እንዳለ ታስታውሳላችሁ? እነርሱም አላስተዋሉትም ነበር። ዛሬስ እንዴት ነው? ዘካርያስ ምዕራፍ 14፡ ሰለ እርሱ መምጣት ይናገራል።

> **በዚያም ቀን እግሮቹ በኢየሩሳሌም ትይዩ፡** እንደገና፡ **በምሥራቅ በኩል ባለው በደብረ ዘይት ላይ ይቆማሉ፡** በ **ደብረ ዘይትም በመካከል** ወደ **ምሥራቅና** ወደ **ምዕራብ ይሰነጠቃል፡ እጅግም ታላቅ ሸለቆ ይሆናል፥... የተራራውም እኩሌታ** ወደ **ሰሜን፡ እኩሌታውም...** ወደ **ደቡብ** ይሰነጠቃል።

**የተራሮችም ሸለቆ** እስከ **አጸል ይደርሳልና፥ በተራሮች ሸለቆ ትሸሻላችሁ፥ እነሆ፡** በ**ይሁዳም ንጉሥ** በ**ዖዝያን** ዘመን **ከሆነው ከምድር መናወጥ ፊት እንደ ሸሻችሁ፡ ትሸሻላችሁ፥...**

97 ምድርን ስንጥቆ የሚከፍት ሌላ የምድር መናወጥ! እዚህ ጋር መጽሐፍ ቅዱስን መከታተል ከፈለጋችሁ፡ በዚህ በ5ኛው ቁጥር ውስጥ አስተውሉ፡ የደብረ ዘይት ተራራ መሰንጠቅ በምድር መናወጥ ምክንያት መሆኑን ያመለክታል፡ ይህ ደግሞ በኢሳይያስ 29፡6 እና ራእይ 16፡9 የተረጋገጠ ነው። በትክክል! ምንድነው? ስለ መጀመሪያው ምጽአቱ የተናገረው ያው ነቢይ፡ ሁለተኛውን ምጽአቱን አይቷል። አስተውሉ፡ "በምድር መናወጥ ዘመን እንደነበረው።" የምድር መናወጦች ምን እያደረጉ እንዳሉ ታያላችሁን? ስለ እነርሱ የተሰጡትን ትንቢቶች ታያላችሁን?

... **አምላ**ካችሁ **እግዚአብሔርም ይመጣል፡ ቅዱሳ**ኑም ሁሉ **ከአንተ ጋር።**

**በዚያም ቀን እንዲህ ይሆናል፡** (ሃሌሉያ) **በዚያ ቀን፡ ያ ብርሃን ብሩህ፡ ወይም ጨለማ አይሆንም፥**

**አንድ ቀንም ይሆናል** እ... **አንድ ቀን ይሆናል እርሱም በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀ ይሆናል፡ ቀንም አይሆንም፡ ሌሊትም አይሆንም፥ ነገር ግን እንዲህ ይሆናል፡** ሲ**መሽ ብርሃን ይሆናል።**

98 አምላክ ሆይ!

ሲመሽ ብርሃን ይሆናል፡

ያው ነቢይ፡ ሕዝቡ ግን ዕውር ነው! መሰህቡ ምንድን ነው? ሁለት ተጨማሪ ቁጥሮችን እናንብብ።

**በዚያም ቀን፡ የሕይወት ውኃ ከኢየሩሳሌም ይወጣል፥ እኩሌታው** ወደ **ምሥራቁ ባሕር፡ እኩሌታውም...** ወደ **ምዕራቡ ባሕር ይሄዳል፥ ይህ** በበጋ **ወቅት እና... ክረምት ይሆናል።** (ወንጌል ወጥቶ ይሄዳል፥ አይሁድም አሕዛብም።)

**እግዚአብሔርም በ... ምድር ሁሉ ላይ ይነግሣል፥** በዚያ **ቀን፡ እግዚአብሔር አንድ፡ ስሙም አንድ** ይሆናል**።**

ሲመሽ ብርሃን ይሆናል፡ (ትክክል!)
የክብርን መንገድ በእውነት ይገኛል፥
በዘመኑ ብርሃን፡ በውኃው መንገድ፡
በኢየሱስ ድንቅ ስም እየተቀበርን።
ወጣት ሽማግሌ፡ ሁሉም ንስሃ ይግባ፡
መንፈስ ቅዱስ በእርግጥ እንዲገባ፥
የምሽቱ ብርሃን መጥቷል፡
እግዚአብሔር እና ክርስቶስ አንድ መሆናቸው ተረጋግጧል።

የት እንዳለን አያችሁ?

አሕዛብ ተበታተኑ፡ እስራኤል ግን ነቃች፡

ነቢያቶቻችን የተነበዩትን ምልክቶች፥ (ይህ የመሬት መንቀጥቀጥ እስከ አሕዛብ፡ እስከ መጨረሻው ቀን ድረስ።)
የአሕዛብ ቀናት ተቆጥረዋል፡ በጭንቀትም ተከበዋል፥
"እናንተ፡ የተበተናችሁ፡ ወደ ዋናችሁ ተመለሱ።"

99 እናንተ የተባረራችሁ ሆይ፡ ታቦቶቹ በአዳዲስ ጋሪዎች ተኝነዋልና፡ ሞት ሳይመታችሁ ከዚያ ውጡ። እግዚአብሔር አረጋግጦታል። እንዲሁ ይሆናል።

100 በብሉይ ኪዳን ወደ ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንሂድ፡ ወደ ሚልክያስ 4ኛው ምዕራፍ፡ ያችንም አጭር 4ኛይቱ ምዕራፍ እናንብባት።

**... እነሆ፡ እንደ ምድጃ እሳት የሚነድድ ቀን፡ ይመጣል፥ ትዕቢተኞችና፡ አዎን፡... ኃጢአትን የሚሠሩ ሁሉ፡** እንደ ገለባ **ይሆናሉ፡...**

101 አሁን፡ ይህ አይደለም... ያ ሚልክያስ 3 ነው፡ እሱም የመጀመሪያው መምጣት ነበረ፡ አሁንም ቀጣዩ መምጣት ይኸው ነው። እዚህ ላይ ዶክተር ስኮፊልድ እንኳ፡ በግርጌ ማስታወሻዎቹ ላይ በእርግጥ ከእሱ ጋር አልስማማም፡ ሆኖም እዚህ ላይ በትክክል አስቀምጦታል። "የዮሐንስ ተልዕኮ"፡ ወደ ሚልክያስ 3፥ እንዲሁም፡ "የክርስቶስ ዳግም ምጽአት፡" ኤልያስም ከአስቀድሞ። እሺ።

... ትዕቢተኞች ሁሉ ያቃጥላ**ሉ፡ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፡ ሥር**ና **ቅርንጫፍ አይተውላቸውም ይላል።** (ታዲያ "ዘላለማዊ" ተብዬው ሲኦል የት አለ? )

**ነገር ግን ስሜን ለምትፈሩት ለእናንተ የጽድቅ ፀሐይ** ትወጣላችኋለች፡ **የፈውስ** ኮንፈረንሶች **በክንፎችዋ ውስጥ ይሆናል፡...** እናንተም **ትወጣላችሁ፡ እንደ ሰባም እምቦሳ፡ ትፈነጫላችሁ።**

**በምሠራበት ቀን በደለኞች፡... ከእግራችሁ ጫማ በታች አመድ ይሆናሉና እናንተ ትረግጡአቸዋላችሁ፡ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።**

አስታውሱ... የባሪያዬን የሙሴን ሕግ አስቡ፡ **በኮሬብ ለእስራኤል ሁሉ፡... ያዘዝሁትን ሥርዓትና** ፍርድን... **አስቡ።**

102 የኤልያስ መምጣት ይህ ነው።

**እነሆ፡ ነቢዩን ኤልያስን** ለእናንተ **እልክላችኋለሁ...**

103 የብሉይ ኪዳን የመጨረሻው መዝጊያ መጽሐፍ ቅዱስ

... **ታላቅና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ** እኔ **ነቢዩን ኤልያስን** ለእናንተ **እልክላችኋለሁ፥**

104 አሁንም፡ ያ ዮሐንስ ሊሆን አይችልም። አይደለም። አያችሁ፡ ዓለም አልተቃጠለችም ጻድቃኑም በክፉዎች ላይ አልተራመዱም። አያችሁ? አይደለም፡ አይደለም።

... **ከታላቁና ከሚያስፈራው የጌታ ቀን** በፊት፥

**መጥቼም ምድርን በእርግማን እንዳልመታ እርሱ የአባቶችን** ልብ **ወደ ልጆች፡ የልጆችንም** ልብ **ወደ አባቶች ይመልሳል፡** ምድርን በእርግማን እንዳልመታ።

105 የመንፈስ ቅዱስን ጥንቃቄ ልብ በሉ፡ እነዚያን ሁለቱን የኤልያስን መምጣቶች አያደበላልቃቸውም። ሚልክያስ 3፡ እንዲህ አለ፡ “እነሆ፡ መልእክተኛዬን በፊቴ እልካለሁ።” ኢየሱስ ስለ ዮሐንስ ተጠይቆ፥ እርሱም እንዲህ አለ፡ “ልትቀበሉትስ ብትወዱ፡ ነቢዩ ‘እነሆ፡ መልእክተኛዬን በፊቴ እልካለሁ’ ብሎ የተናገረው ይህ ነው። ሊመጣ ያለው ኤልያስ ይህ ነው።” ሚልክያስ 3።

106 መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት በጥንቃቄ እንደሚያስቀምጠው ልብ በሉ። ይህ ምን እንደሆነ... ማመን ለሚፈልጉ፡ ማየት ለሚሹ... ይሄን ለማሳየት። ኢየሱስ በቅዱስ ቃሉ አጋማሽ ላይ ማቆሙን፡ ትዝ ይላችኋል፡ ምክንያቱም ከፊሉ በዚያን ጊዜ ተፈጽሞ ነበር፡ ቀሪው ግን ለዳግም ምጽአቱ እንደሆነ? “የተወደደችውን የጌታን ዓመት ለመሰበክ፡ ልባቸው የተሰበረውንም ለመጠገን”፡ አቆመና፥ እስከ ዳግም ምጽአቱ ድረስ “ለአሕዛብ ፍርድን ለማምጣት” አይደለም።

107 ይህ ቅዱስ ቃል እዚህ ላይ ከእሱ ጋር እንደሚመሳሰል ልብ በሉ። “እርሱም፡ ኤልያስ፡ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች ይመልሳል።” (አሁን ስለ ሚልክያስ 4 እየተናገረ ነው፡ ከሚልክያስ 3 ጋር፡ እንዳታደባልቁት።) ዮሐንስ፡ ኤልያስ፡ ከክርስቶስ የመጀመሪያ መምጣት በፊት በነበሩት ቀናት የመጣው፡ የቀድሞ አባቶችን ልብ ወደ ልጆቹ መልእክት፡ ወደ አዲሱ መልእክት መለሰ።

108 አሁን ተመልከቱ። “የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች።” በዳግም ምጽአቱ፡ በመጨረሻዎቹ ቀናት፡ እንደገና ወደ ሐዋርያዊው እምነት ይመልሳል። ቅዱሳት መጻሕፍት ምን ያህል ፍጹም እንደሆኑ አያችሁ?

109 ያ የብሉይ ኪዳን፡ የብሉይ ኪዳን ፍጻሜ ነበረ። አሁን በዚህ በምሽቱ ጊዜ ብርሃን እንዳለ እያየን ነው። እርሱ ምንድን ነው? እርሱ ጫፉ፡ የዛፍ ከፍተኛ ጫፍ ነው።

110 ዛሬ ጠዋት እንደተናገርኩት፡ እኛ የመጣነው በየሐይማኖት ተቋማት ውስጥ አልፈን ነው፡ በ (የብርቱካን ዛፍ ያይደለ) ዛሬ ጠዋት እንደተናገርኩት፡ ነገር ግን ግሬፕፍሩት፡ ሎሚ፡ ከመጀመሪያው ፈጽሞ የማይመሳሰሉ ሌሎች ነገሮች ሁሉ ነበሩን። ሆኖም በኋላ... እንዳያመልጣችሁ። እነሆ መጣ። የሐይማኖት ተቋማት ሁሉ አብኩተው ካበቁ በኋላ፡ ከጅምሩም ምንም ብርሃን አልነበራቸውምና፡ እነሆም ቀንም ሌሊትም ተብሎ ሊጠራ የማይችል ቀን ይመጣል።

111 ምን እያደረጉ ነው? ምን እያደረጉ ነው? ሎሚ በብርቱካን ዛፍ ላይ—ምን ያደርጋል? የሚመጣውን የብርቱካኑን የመጀመሪያ ሕይወት ይቀበልና ወደ ሎሚነት ያጣምመዋል። የሐይማኖት ተቋማት በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያደረጉት ያንን ነው፡ የእግዚአብሔርን ቃል በትውፊቶቻቸው ከንቱ አደረጉት። ይህ **የጌታ መንፈስ እንዲህ ይላል** ነው። ሎሚዎችን፡ የወይን ፍሬዎችን ያፈራሉ፡ እንጂ ብርቱካን አይደለም።

112 ዳሩ ግን ነቢዩ ምን አለ? ዛሬ ማታ ለርዕሳችን የተናገረው ያው ነቢይ፡ “እናንተ የኢየሩሳሌም ቈነጃጅት፡ ደስ ይበላችሁ፡ የጽዮንም ቈነጃጅት ሆይ፡ እልል በሉ፡ እነሆ ንጉሳችሁ፡ ገርና ትሑት ሆኖ፡ በአህያይቱና በውርንጫይቱ

ላይ ተቀምጦ ወደ እናንተ ይመጣል፡" ያው ነቢይ እንደተናገረው፡ "ሰብል የሚበሰልበት ጊዜ ይመጣል" ማለቱን ልብ በሉ። ፍሬውን ለማብሰል በምድር ላይ የተላከችው ፀሐይ ናት። ለምን ሊበሰል አልቻለም? የሚበሰል ፍሬ እዚያ የለምና። ሆኖም ሕይወት አሁንም ጉዞዋን ቀጥላለች።

113 ብርቱካን ለመሆን፡ በግሬፕፍሩት መጣ፡ ከዚያም የተደራጀ መሆኑን ሲያውቅ፥ ግሬፕፍሩት ነው። እንደገናም ሄደ፡ በዚያን ጊዜም ሎሚ ሆኖ ወጣ። እንደገና ቀጠለ፡ ሌላ ነገር ሆነ። በመጨረሻም፡ በዛፉ ጫፍ ላይ፡ ታንጀሎ ሆነ፡ እሱም ግማሽ ብርቱካን፡ ግማሽ ሎሚ ነው፥ የተቀላቀለ ዝርያ፡ የተበላሸ ነገር፥ በዚያው ዛፍ ላይ እየኖረ፡ ወደ መበላሸት የመጣ፥ ቅርፊቱ፡ "የተመረጡትን እንኳ ሊያታልል።" ብርቱካን ይመስላል፡ ነገር ግን አይደለም።

114 እሷ ድርጅት ከመሆን በላይ አልፋ ስታድግ ግን፡ "እነሆ ብርሃን ይሆናል።" ድርጅት ከመሆን ስታልፍ፡ እንደገና ታብባለች፡ ልክ ወደ ምድር እንደገባው ብርቱካን ታፈራለች፡ ከዚያም ብርሃን ይሆናል።

115 ይህ መሰህብ ምንድን ነው፥ ይህስ ክስተት ምንድን ነው? የእግዚአብሔርን ቃል መፈጸም። ይህ እንደሚሆን፡ የብሉይ ኪዳን ሁለት ምስክሮች አሉ።

116 ከአዲስ ኪዳን፡ የዮሐንስ ወንጌል 14፡12ን እንውሰድ፡ ኢየሱስ እንዲህ አለ።

> **... በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፥...**

117 እንዲሁም፡ በሉቃስ 17፡22 እስከ 30 ላይ፡ እርሱ እንዲህ አለ፥

> ... በሎጥ ዘመን እንደነበረው፥ ሰዶም ከመቃጠሏ በፊት፡ የሰው ልጅ በሚመለሰበት ዘመን፡ **የሰው ልጅ በሚገለጥበት** በዚያ **ቀን እንዲሁ ይሆናል።**

118 ኦህ፡ መጽሐፍ ቅዱሰን ተመልከቱ! "የሰው ልጅ፡" ኢየሱስ ክርሰቶሰ ትናንትና፡ ዛሬም፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው፡ ከየሐይማኖት ተቋማት አልፎ አደገ፡ ወደ ዛፉ ጫፍ ድረሰ አደገ። በዮሐንስ 14፡ ወይም 15 ላይ ምን አለ? "በእኔ ያለውን ፍሬ የማያፈራውን፡ ቅርንጫፍ ሁሉ፡ ይቆርጠዋል ይከረከማል፡ ወደ እሳትም ተጥሎ ይቃጠላል። ነገር ግን ፍሬ የሚያፈራውን ቅርንጫፍ ሁሉ፡ ያጠራዋል።"

119 ኦህ፡ በመጨረሻዎቹ ቀናት ከእርሱ ጋር በመጣችው ትንሿ መንጋ ላይ እውነተኛ የሆነ ፊተኛ እና የኋለኛው ዝናብ ይወርዳል፡ ገር እና ትሑት ሆና፡ ም-... ምንም ዓይነት የሐይማኖት ተቋም ሳይኖርባት፡ እንዲህ ብላ በምትጮኸው ይወርዳል፡ "በጌታ ሰም ለሚመጣው ንጉሥ ሆሳዕና!" ዛሬ ችግሩ ምንድነው? በተራራው ላይ ያለው መሰህብ ምንድነው?

120 በቅርብ ጊዜ፡ በዚህ መድረክ ላይ ቆሜ ሳለሁ፡ በመንፈሰ ቅዱሰ እንዲህ ተብሎ ነበር፡ "በቤትህ ፊት ለፊት እንጨት የሚተክሉበት ቀን ይመጣል፥ በርህንም ያንቀሳቅሱታል። ሰለዚህ፡ በዚያ፡ እንዳትቆጣ፡ አልፈኸው ሂድ።" በሬ ተነቅሎና በተራራው ላይ ተጥሎ አየሁ። ከፊቴ ያለው ኮረብታ፡ ተቆፍሮ፡ ሳንቃዎችና ነገሮች የሆነ ነገር ሰባብሯቸው በዚያ ተጋድመው አየሁ። እርሱም አለ...

ተመለከትኩ፡ እነሆም አንድ ትንሽ ወጠጤ ወደዚያ ወጥቶ በሩን ሰብሮት፡ እንዲህ አድርጎት ነበር። እኔም፡ “ለምን አልነገርከኝም” አልኩት? እርሱም በትዕቢት መለሰልኝ፡ ልመታውም ተገደድኩ። ይህንንም በሆነ ጊዜ፡ “በቦክስ ሜዳ ላይ ከነበርኩበት ጊዜ ጀምሮ ይህን አድርጌ አላውቅም፡ ቢሆንም እንድታውቀው እፈልጋለሁ፡” አልኩትና፡ አንድ ጊዜ ነረትኩት። በዘረርኩትም ጊዜ፡ እንደገና አንሥቼ ድጋሚ ዘረርኩት። ሦስት ወይም አራት ጊዜ፡ አንሥቼ፡ ከዚያም በተራራው ላይ አሳደድኩት። ከዚያም ወደዚያ ወጥቼ፡ “ይህ ትክክል አይደለም፡” አልሁት። እንሥቼውም እጁን ጨበጥኩትና፡ ተናገርኩት፡ “እኔ በአንተ ላይ አልተበሳጨሁብህም፡ ነገር ግን እንደዚህ ልታናግረኝ እንደማትችል እንድታውቅ እፈልጋለሁ” አልኩት።

ከዚያም ዘወር ብዬ ስመለስ፡ መንፈስ ቅዱስ በበሩ አጠገብ ቆሞ ነበር፡ እንዲህም አለ፡ “አሁን ይህንን አልፈኸው ሂድ። ያ እንጨት በሚተከልበት ጊዜ፡ ወደ ምዕራብ ዞር በል።”

> የሚያስፈልገኝ፡ ይህ መጽሐፍ ነው፡
> መጽሐፉ ጥሩ የምግብ አሰራር ነው፡
> ከችግሬ የምወጣበትን መንገድ ያሳየኛል። አሜን!

121 ያም መጽሐፍ ቃል ነው፡ ያም ቃል እግዚአብሔር ነው። ችግሮቻችሁን አልፋችሁ ሂዱ፡ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ እርሱ ይነግራችኋል።

122 ከሦስት ዓመት በፊት፡ የከተማው የመሬት ቀያሽ የሆነ፡ ከቤቴ ዝቅ ብሎ ባለው መንገድ ላይ የሚኖር ጓደኛዬ፡ እንጨት ሲተክል ሰማሁ። ወደዚያ ወጥቼ፡ “ምን ሆነሃል፡ ማድ” አልኩት? የአቶ ኪንግ ልጅ፡ የቅርብ ጓደኛዬ ነው።

እርሱም፡ “ቢሊ፡ ይህንን መንገድ ሊያሰፋፉት ነው” አለኝ።

123 ሁላችሁም ታስታውሳላችሁ። “ምናልባት ድልድዩ ሊሆን ይችላል፡” አልኩ። ለወንድም ዉድ፡ እንዲህ አልኩት፡ “ንብረትህን ያዝ። ምናልባት ያ ድልድይ እዚህ ላይ ያልፍ ይሆናል፡ ወይም ሌላ ነገር” አልኩት። መንገዱ ተበላሽቶ ነበር፥ ጡቦች፡ ድንጋዮች፡ በሁሉም ነገር ላይ ተጥለው ነበር። ስለዚህ እርሱን... አልኩት፡ “ይዞታህን አትልቀቅ።” ከዚያም እ...

አቶ ኪንግ ይህ እንደሚሆን ነገረኝ።

124 ወደ ውስጥ ገብቼ፡ ማዶ ለተቀመጠችው ሚስቴ እንዲህ አልኳት፡ “ውዴ፡ ስለዚያ የተጻፈ ነገር አለ። በሆነ ሰፍራ፡ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**” የሚል አለ።

125 ገብቼ ማስታወሻዬን አወጣሁ፡ ፈተሽኩትም፡ እንዲህም ይል ነበር፡ “እነሆ እንዲህ ይሆናል... ” ከሰምንት ዓመታት በኋላ!

126 ከዚያም ባየሁት ጊዜ፡ “አሁን ጊዜው ደርሷል፡ ውዴ፡ ወደ ምዕራብ መሄድ አለብን፡” አልኳት።

127 ከዚያ ከሁለት ቀናት በኋላ፡ አንድ ቀን ጠዋት በአራት ሰዓት ገደማ፡ በክፍሉ ውስጥ ቆሜ ሳለሁ ወደ እግዚአብሔር መንፈስ ገባሁ። በህብረት የሚበሩ የእርግቦች መንጋ አየሁ፡ ትናንሾቹ ወፎች ተመለከትኳቸው። ታስታውሳላችሁ። ሰባት መላእክትን በፒራሚድ መልክ፡ ወደ እኔ በፍጥነት ሲመጡ አየሁ። አሉኝም፡ “ወደ ምዕራብ ዞር በል፡ ወደ ቱሳን ሂድ፡ አርባ ማይል በሰሜን

ምሥራቅ በኩል ሁን። ከልብሰህም ላይ አሜከላ፡” ወይም፡ ቡልሄደር ይሉታል በዚያ፡ “ትለቅማለህ።”

128 ወንድም ፍሬድ ሶትማን፡ ልክ አሁን እዚህ ተቀምጦ የሚመለከተኝ፡ በዚያ ጠዋት በዚያ ነበረ። ረሰቼው ነበር።

129 እኔም፡ “በሀገሪቱ ያለውን ነገር ሁሉ ያናወጠ፡ እንደ ምድር መንቀጥቀጥ ያለ ታላቅ ፍንዳታ ተሰማ። ሰው እንዴት ከዚያ ሊተርፍ እንደሚችል አልገባኝም” አልኩ። ፈርቼ ነበር። በፊኒክስ ቆሜ ነበር፡ ዛሬ ማታ የምታደምጡኝ ሁሉ ምስክሮቼ ናችሁ። በሰብከቴ ላይ እንዲህ የሚለውን ሰበክሁ፡ **ጌቶች ሆይ፡ ሰዓቱ ስንት ነው?** “የት ላይ ነን? ” ወደ ምዕራብ ሄድኩ። ብዙዎቻችሁ እዚህ ያላችሁት ቅጂው ደርሶአችኋል፡ ብዙዎቻችሁ ይህ ከመሆኑ በፊት፡ ከአንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ በፊት ሲነገር ሰምታችኋል።

130 ምን ሊከሰት እንደሚችል እያሰብኩ፡ ወደ ምዕራብ ሄድኩ። በአንድ ወቅት ከጌታ ጥሪ ደረሰኝ። ለባለቤቴ ነገርኳት፡ እንዲህ አልኳት፡ “የኔ ማር፡ ም... ምናልባት ሥራዬ አብቅቷል።” እኔ አላወቅኩም ነበር። እንዲህም አልኳት፡ “እ... እግዚአብሔር፡ እግዚአብሔር ምናልባት በእኔ ላይ ሥራውን ጨርሷል ወደ ቤቴም መሄዴ ይሆናል። አንቺ ከቢሊ ጋር ሁኚ፡ ልጆቹንም ውሰጂ። እግዚአብሔር በሆነ መንገድ፡ መንገድ ያዘጋጅልሻል። ቀጥለሽ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነሽ ኑሪ። ልጆቹ ትምህርታቸውን እንዲጨርሱ አድርጊ፡ በእግዚአብሔርም ምክር አሳድጊያቸው” አልኳት።

እሷም፡ “ቢል፡ ያ ትክክል መሆኑን አ—አታውቅም” አለችኝ።

“አይ፡ ቢሆንም ሰው ከዚያ ሊተርፍ አይችልም፡” አልኳት።

131 አንድ ቀን ጠዋት ጌታ አነቃኝ፡ እንዲህም አለኝ፡ “ወደ ሳቢኖ ገደል ወደላይ ውጣ።” አንድ ወረቀትና መጽሐፍ ቅዱሴን አነሳሁ።

ሚስቴም፡ “ወዴት ነው የምትሄደው” አለችኝ?

እኔም፡ “አላውቅም። ስመለስ እነግርሻለሁ” አልኳት።

132 ወደ ገደሉ ወጣሁ፡ ንሰሮች ወደሚበሩበት ጫፍ ላይ ወጣሁ። እዚያ የቆሙትን አጋዘኖች እመለከት ነበር። ለመጸለይ ተንበረከክሁ፡ እጆቼንም አነሳሁ፡ አንድ ሰይፍም እጄን መታኝ። ዙሪያዬን ተመለከትኩ። እንዲህ ብዬም አሰብኩ፡ “ይህ ምንድን ነው? መቼም አላበድኩም። ይኸው ሰይፉ በእጄ ላይ ነው፥ ደማቅ፡ የሚያበራ፡ በፀሐይ ላይ የሚያንጸባርቅ ሰይፍ።” እኔም፡ “አሁን፡ በዚህ ገደል እጅግ ርቀት እንኳን፡ ምንም ሰው የለም። ይህ ከየት ሊመጣ ይችላል” አልኩ?

አንድ ድምፅ፡ እንዲህ ሲል ሰማሁ፡ “ይህ የንጉሡ ሰይፍ ነው።”

እኔም፡ “ንጉሥ ሰውን በሰይፍ ሹም ያደርጋል” አልኩ።

133 እርሱ፡ ያ ድምፅ፡ ተመልሶ፡ እንዲህ አለ፡ “የማንም ንጉሥ ሰይፍ አይደለም፡ ይህ ግን፡ ‘የንጉሡ ሰይፍ፡’ የጌታ ቃል ነው።” እርሱም፡ “አትፍራ። ይህ ሦስተኛው ሰህበት ነው። የአገልግሎትህ ማረጋገጫ ነው” አለኝ።

134 ምን እንደሚከሰት ሳላውቅ፡ ከአንድ ጓደኛዬ ጋር ለማደን እየሄድኩ ነበር።

የጌታ መልአክ ሰዕልን በተመለከተ የነቀፈኝና፡ ፎቶውን ያነሳው ሰውዬ፡ ደወለልኝ። ልጁ የሞት ፍርድ ተፈርዶበት፡ ከጥቂት ቀናት በኋላ ሊገደል ስለነበር ወደ ሂውስተን መሄድ ነበረብኝ። በዚያም አግኝቶኝ እቅፍ አደረገኝና፡ አለም፡ "እሰቲ አሰበው፡ የነቀፍኩት ሰውዬ ብቸኛ ልጄን ሊያድን መጣ!" የሰብአዊ መብት ድርጅት፡ ሕይወት በማዳኔ፡ ኦስካር ይሁን ወይም የሆነ ብለው የሚጠሩትን ሽልማት ሰጡኝ።

135 ከዚያም ተመለስን፡ ለማደን ወደ ተራራው ወጣሁ። በዚያ፡ አንድ ጠዋት፡ ከወንድም ፍሬድ ጋር አብረን ሰወጣ፡ ቀደም ሲል የዱር አሳማዬን አ— አግኝቼ ስለነበር፡ እነርሱ የሄዱበትን ቦታ አይቼ ተመለከትኩ። እንዲህ አልኩት፡ "ወንድም ፍሬድ፡ ነገ ማለዳ ጎህ ሲቀድ፡ ወደዚያ ተራራ ሂድ፡ እኔም በሌላኛው ላይ እሆናለሁ። በአሳማው ላይ አልተኩሰም፡ አልገድለውምም። ነገር ግን መንጋው፡ ወደዚህ አቅጣጫ መምጣት ከጀመረ፡ ከፊታቸው እተኩሰና ወደ ኋላ እመልሳቸዋለሁ።"

136 ወንድም ፍሬድ ወደዚያ ሄደ ነገር ግን ምንም አሳማዎች አልነበሩም። እጁን አወዛወዘልኝ ተመለከትኩም። ወደ ገደሉ ውስጥ፡ ወደ አንዳንድ ትላልቅ ገደላማ ሰፍራዎች ወረድኩ፡ ፀሐይም ገና እየወጣች ነበር። ሰለ ትንቢቶቹ ምንም ሳላሰብ፡ በተራራው በሌላኛው በኩል ዞርኩ። ተቀምጬ፡ እየጠበቅኩ፡ እያረፍኩ፥ "እነዚያ አሳማዎች ምን ሆነው ይሆን፡" ብዬ አሰብኩ?

137 የነበረኝ ነገር አነሳሁና... እንደ ሕንዶች፡ እግሬን-አጣጥፌ፡ ተቀመጥኩ። ቱታዬን ተመለከትኩትና፡ አሜኬላ ሞልቶት ነበር። ለቀምኩት። ከራሴም ጋር፡ "ይህ እንግዳ ነገር ነው! እዚህ፡ ቱሳን በሰሜን ምሥራቅ አርባ ማይል ገደማ ላይ ነኝ። ትንሹ ልጄ ጆሴፍ በዚያ ተቀምጦ እየጠበቀኝ ነው።" መመልከት በጀመርኩበት ጊዜ፡ ከተራራው ላይ፡ በአንድ ሺህ ያርድ ገደማ ርቀት ላይ የአሳማ መንጋ ሲወጣ አየሁ፡ አሜኬላውን አራገፍኩት። እንዲህም አልኩ፡ "አገኛቸዋለሁ። ወንድም ፍሬድን ፍለኣ እወጣለሁ፡ ወዴት መሄድ እንዳለብን የሚገልጽ ወረቀት፡ በዚች ጭራሮ ላይ እሰቅላለሁ፡ ወንድም ፍሬድንም እናገኘዋለን።"

138 በሌላኛው በኩል በሙሉ ኃይሌ እየሮጥኩ፡ ወደ ተራራው መውጣት ጀመርኩ። ድንገትም፡ አንድ ሰው ተኩሶ የመታኝ መሰለኝ። እንደዚህ ያለ ፍንዳታ ሰምቼ አላውቅም፥ መላ ሀገሪቱን አናወጠ። እናም፡ ይህ በሆነ ጊዜ፡ ሰባት መላእክት በቡድን ሆነው በፊቴ ቆመው ነበር።

139 ከአፍታ ጊዜ በኋላ፡ ከወንድም ፍሬድና ከሌሎቹ ጋር ተገናኘን። "ምን ነበረ፡" ብለው ጠየቁኝ?

እኔም፡ "ያ ነበር" አልኳቸው።

"ቀጣይ ምታረገው ነገር ምንድነው? "

140 "ወደ ቤት መመለሰ። ምክንያቱም፡ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፡ በእነዚህ ሁሉ ዓመታት በመጽሐፍ ቅዱሰ ውሰጥ የተሰወሩ ሰባቱ ምሥጢራት፡ እነዚህ የሃይማኖት ተቋማት እና ሌሎች ነገሮች ሁሉ፡ እግዚአብሔር በሰባት ማኅተሞች ውሰጥ እነዚህን ሰባት ምሰጢሮች ይፈታልናል።"

141 ከምድር እንደሚወጣ ልክ እንደ ጉም የተፈጠረ፡ ያ ክብ ነገር መጣ። ይህ በሆነ ጊዜም፡ በቀጥታ ወደ ተራራው ወጣ፡ ከመጣበት አቅጣጫ፡ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ መዞር ጀመረ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ ሳይንስ ሠላሳ ማይል ከፍታና ሃያ-አምስት ማይል ስፋት፡ በትክክል በፒራሚዱ ክብ ቅርጽ ውስጥ ደረሱበት።

142 በቅርቡም፡ በዚያ ቆሜ ሳለሁ፡ ፎቶውን ወደ ቀኝ ሳዞረው፡ በሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመናት እንደነበረው፡ ነጭ ዊግ እንዳደረገው ኢየሱስ ነበር፡ ይህም ፍጹም መለኮትነቱን ያሳያል። አልፋ እና ኦሜጋ ነው፥ ፊተኛውና ኋለኛው እርሱ ነው፥ እርሱ የዚህን ዘመን መልእክት ለማጽናት የቆመ፡ የዘላለም ሁሉ ፍጹም ፈራጅ ነው። ሲመሽ ብርሃን ይሆናልና! ይህ ሁሉ ስለ ምንድነው? ምንስ ነበር?

143 ወደ ምዕራብ ሄድኩ። በዚያው ተራራ ላይ፡ ከባንክስ ዉድ ጋር እያለፍኩ ሳለሁ፡ እንዲህ አለ፡ "ድንጋይ ወደ ላይ ወርውር። ለአቶ ዉድ እንዲህ በለው፡ 'የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ የእግዚአብሔርን ክብር ታያለህ።"

144 በማግስቱ፡ በዚያ ቆሜ ሳለሁ፡ አውሎ ነፋስ ወደ ታች ወረደና ተራራዎቹን ሰባበራቸው። ከጭንቅላቴ በላይ ከሦስት ወይም ከአራት ጫማ ከፍታ ላይ፡ ድንጋዮች የዛፎቹን ጫፎች ቆራረጧቸው። ሦስት ታላላቅ ፍንዳታዎች ተሰሙ፡ ወንድሞችም እየሮጡ መጡ። በዚያ አሥራ አምስት ገደማ ሰዎች ቆመው ነበር፡ እነርሱም ሰባኪዎችና ሌሎችም ነበሩ። "ምን ነበር? " "ምንድነው፡" አለኝ?

"ምእራባዊ ጠረፍን በፍርድ እየመታ ነው፡" ብዬ ተናገርሁ።

145 ከዚያ ከሁለት ቀናት በኋላ፡ የምድር መንቀጥቀጡ አላስካን ሊያስጥማት ጥቂት ቀረው። በአሪዞና በኮሮናዶ ጫካ ውስጥ በሳንሴት ተራራ ላይ ያለው ይህ ብርሃን ምንድን ነው? ሰዎች ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ እየነዱ፡ ያ ብርሃን በወረደበት ስፍራ የተበተኑትን ድንጋዮች እየለቀሙ ያሉት፡ ይህ እዚያ ላይ የተከሰተው እንግዳ ነገር ምንድን ነው? እያንዳንዱም ድንጋይ፡ እያንዳንዱ፡ የተሰበረው ድንጋይ፡ ሦስት ማዕዘን ነበረው። (ሦስቱ አንድ ናቸው።) በመላ አገሪቱ፡ በጠረጴዛዎች ላይ፡ በወረቀት መጫኛዎች ላይ ተቀምጠዋል። በኮሮናዶ ጫካ ውስጥ በሳንሴት ተራራ ላይ የታየው ይህ እንግዳ ነገር ምንድን ነው?

146 በማዳመጣ ላይ ያለኸው ጁኒየር ጃክሰን፡ እርሱ ያየውን እኔም እንዲህ ብዬ የተረጎምኩትን ሕልም፡ "ወደ ፀሐይ መግቢያ መሄድ" ታስታውሳላችሁ? ይህም የተከሰተው በ "ሳንሴት" ተራራ ላይ ነው። የምሽቱ ጊዜ፡ የጸሐይ መጥለቂያ ሰዓት ነው። የጸሐይ መጥለቂያ መልእክት በታሪክ መገባደጃ ውስጥ፡ ማለቴ፡ በትንቢት መገባደጃ ውስጥ፡ የተፈጸመ። በምሽቱ ጊዜ ብርሃን ይሆናል፡ በቱሳን ሰሜን አርባ ማይል ርቀት ላይ ባለው በኮሮናዶ ጫካ ውስጥ፡ በሳንሴት ተራራ ላይ ሆነ። በካርታው ላይ ተመልከቱና በዚያ የሳንሴት ጫፍ መኖሩን እዩ። በትክክል የተከሰተው በዚያ ነው። እስከ ቅርብ ቀን ድረስ ፈጽሞ አላወቅኩትም ነበር።

147 ያ ሁሉ... ያ ከቶ አይሞትም። እርሱ በተደጋጋሚ ራሱን ይገልጣል። ከተከሰተው ነገር ጀምሮ፡ እኛን እያየን የቆመው የኢየሱስ ምስል እስከሆነው ድረስ፥ አሁን ደግሞ በትክክል በሳንሴት ተራራ ላይ፡ የጸሐይ መጥለቂያ ብርሃን ታየ። የምሽቱ ብርሃን መጥቷል፡ እግዚአብሔር ራሱን እያረጋገጠ ነው። ምንድን ነው? እግዚአብሔር እና ክርስቶስ አንድ መሆኑ ተረጋግጧል። በራእይ

1 ላይ እንደተነጋገርነው፡ “ነጭ፡” በራሱ ላይ የነበረውን ነጭ ዊግ፡ ስንቶች አይታችሁታል? ይህም፡ ልዑል አምላክነቱ፡ የበላይ ስልጣን፥ ሌላ ድምጽ፡ ሌላ አምላክ፡ ሌላ ነገር አይደለም! “በእርሱ የመለኮት ሙላት በሰውነቱ ተገልጦ ይኖራል።” መላእክት ራሳቸው የእሱ ዊግ ነበሩ። አሜን።

148 በሳንሴት ተራራ ላይ ምን ተከሰተ? እግዚአብሔር ቃሉን እያረጋገጠ ነበር። ይህ ሁሉ ጩኸት ስለዚያ ነው። አስተውሉ፡ እግዚአብሔር የተሰፋ ቃሉን እንደገና እየፈጸመ ነው፡ የራዕይ 10፡1 እስከ 7 ላይ፡ “የሰባተኛውም መልአክ መልእክት በሚያሰማበት ዘመን፡ የእግዚአብሔር ምሥጢር ይፈጸማል።” የራእይ 10፥1 እስከ 7 የተሰወረው ምስጢር፡ ለመጨረሻዋ የቤተክርስቲያን ዘመን የተሰጠው የመጨረሻው መልእክት ነው። በዚህ ዘመን፡ በቅዱስ ሉቃስ 17፥30 ላይ ያለውን፡ በትክክል ይፈጽማል፡ “የሰው ልጅ በሚገለጥበት ቀን።”

149 “ሐሰተኞች ነቢያትና ሐሰተኞች ክርስቶሶች ይነሣሉና፡ ቢቻል ኖሮስ የተመረጡትን እንኳ እስከሚያስቱ ድረስ፡ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ።” ሕዝቡ አሁንም በመጠራጠር ላይ ነው። እንግዲህ፡ እንደ ወትሮው፡ ቤተክርስቲያኗ በተመሳሳይ ሁኔታ ግራ ተጋብታለች።

150 ሳይንሰም፡ በመላው ቱሳን ውስጥ፡ ጽሑፎችን እየጻፉ በጋዜጣ ላይ እያወጡት ነው። በሌመን ተራራ በስተጀርባ፡ እነዚያ ታላላቅ ካሜራዎች እኛ በቆምንበት ስፍራ ሲነሳ አላዩትም፥ ጊዜው ማብቃቱን እያሳየ፡ ወደ ምዕራብ ይንሸራሸር ነበር። ሆኖም በዚያ ጥቂት ርቀት ብቻ እንጂ መቀጠል አይችልም፥ በምዕራባዊው ዳርቻ ላይ ነው። ፍርዱም በሄደበት መንገድ ላይ ወረደ። በፊኒክስ ላይ አልፎ ቀጥታ በመሄድ፡ ወደ ፕሬስኮት እንዲሁም በተራራዎቹ ላይ ወደ ምዕራባዊው ዳርቻ፡ ቀጥታ ወደ... ወዴት እየሄዱ ነበር? ቀጥታ ወደ አላስካ፡ እርሷም እያንጎዳጎደች፡ ወደዚያ አቅጣጫ እያመራች ነው።

151 በቱሳን ያሉት የዳሰሳ ጣብያዎች ሁሉም አሁንም እየጠየቁ ነው፡ የሳይንስ ምርምርም ምን እንደሆነ ለማወቅ እየሞከረ ነው። እዚያ ላይ ጭጋግ፡ ጉም፡ ወይም ምንም ነገር ሊሆን በማይችልበት እጅግ ከፍተኛ ከፍታ ላይ ነው። “ምን አደረገው? የት ነው ያለው? ” ሰማይ ላይ የታየው ከተፈጥሮ በላይ የነበረው የብርሃን ጸዳል እያዩ ሰብአ ሰገል ኮከብን ተከትለው ሲመጡ እንዳሉት፡ አሁንም ግራ ተጋብተዋል፡ “የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ” እርሱ ምን ነበረ? እግዚአብሔር ቃሉን ሲፈጽም ነው፡ “ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል።”

152 የሰማይም አምላክ ሲመሽ የማምሻው ብርሃናት እንደሚሆኑ ተሰፋ ሰጥቶ ነበር። ከሦስት ዓመት በፊት ይህ ምስጢር፡ “ጌታዬ፡ ሰንት ሰዓት ሆነ” የሚል ትንቢት ነበረ? አሁን ግን ታሪክ ሆኗል ። አልፏል። የተሰፋው ቃል ተፈጽሟል። ሰንት ሰዓት ሆነ፡ ጌታዬ፡ ይህስ መሰህብ ምንድን ነው? እግዚአብሔር ቃሉን ሲፈጽም ነው! እሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እና ለዘላለም ያው ነው።

እንጸልይ።

153 የተወደድክ አምላክ ሆይ፡ ካሰብኩት በላይ ሰዎችን፡ እጅግ አቆይቻቸዋለሁ። አምላክ ሆይ፡ በሁሉም ስፍራ ያሉ ሰዎች እንዲረዱት እንዳች የተነገረ ወይም የተደረገ ነገር እንዲኖር፡ እጸልያለሁ። በማየትና በመረዳትም አንተ እውነተኛው ክርስቶስ መሆንህን፡ እየተረጋገጡ ያሉት ቃላት

ደግሞ ቃሉ ፍጹም መሆኑንና በጊዜው መፈጸሙን ማረጋገጫ መሆናቸውን ያምኑ ዘንድ እጸልያለሁ።

154 አሁንም፡ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ከአንተ ራስህ ቃላት፡ ዓለም በሰዶም ሁኔታ ውስጥ እንደምትሆን ተናግረሃል። ያንን እናውቃለን፡ ልንመለከተውም ችለናል። አንተም፡ በዚያ ቀን፡ “በሰዶም እንደነበረው” ብለሃል። ደግሞም ለአሕዛብና ለዕብራውያን ዓለም የተላኩ ሦስት መልእክተኞች ነበሩ። ከእነርሱም አንዱ፡ እግዚአብሔር ራሱ፡ የሰው ልጅ፡ ራሱን በሰው አምሳል ገልጦ ተአምር አደረገ፡ ሳራም በስተጀርባው በድንኳኑ ውስጥ ምን እያደረገች እንደነበረ ለአብርሃም እስከመናገር ደረሰ።

155 መላው የአሕዛብ ዓለም በሰዶም ሁኔታ ውስጥ በሚሆንበት ጊዜ ይህ እንደገና እንደሚደገም ተናግረሃል። እኛም እነሆን፡ ጌታ ሆይ። ሌሎች ትንቢቶችም ያንኑ ነገር ያረጋግጣሉ፡ ማለትም በመጨረሻዎቹ ቀናት ኤልያስን ስለ መላክ፡ የኤልያስን መንፈስ በምድር ላይ ስለ መላክ፡ የአባቶችን ልብ፡ ወይም፡ “የልጆችን ልብ ወደ አባቶች ለመመለስ።” አምላክ ሆይ፡ በዚህ ሰዓት ቃልክን እንድታጸና፡ አንተ ትናንት፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም፡ ያው መሆንህን እንድታሳይ እጸልያለሁ። ይሁን፡ አባት ሆይ። ሁሉም የአንተ ናቸው። እነዚህን በረከቶች እንድትሰጥ እና የተነገረውን እንድታረጋግጥ፡ ለእግዚአብሔር ክብር ይህ እንድትሰጠን እጸልያለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

156 ቃልን መናገር፡ የሰው ነው፥ ቃልን ማረጋገጥ ግን፡ የእግዚአብሔር ድርሻ ነው። አንድ ነገር መናገር፡ አንድ ነገር ነው፥ እግዚአብሔር እንዲያደርገው ግን፡ ሌላ ነገር ነው። እግዚአብሔር ተርጓሚ አያስፈልገውም፥ ራሱን እርሱ ራሱ ይተረጉመዋል።

157 አሁን የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆን፡ ለሕመምተኞች የምንጸልይበትን፡ የጸሎት መሰመር ለማዘጋጀት እያስተካከልን ነው። እናንተን ሊፈውስ የሚችለው፡ ወንድ፡ ወይም ሴት፡ ሰውም ይሁን፡ መልአክም ይሁን፡ አንዳች እንደሌለ እናውቃለን፡ እግዚአብሔር አስቀድሞ ፈውሷችኋልና። ዝግጅቱን አጠናቋል፡ ከእናንተ የሚጠበቀው መቀበሉ ብቻ ነው።

158 ኃጢአቶቻችሁን ይቅር ሊል የሚችል፡ ማንም ሰው፡ መልአክ፡ ወይም ሌላ ምንም ነገር የለም፡ እግዚአብሔር ራሱም ቢሆን፡ ምንም የለም። አስቀድሞ ተደርጓል። ኢየሱስ በመሰቀል ላይ ያንን አድርጓል። ሆኖም እስክትቀበሉት ድረስ ምንም አይጠቅማችሁም፡ ወይም ምንም ጥቅም አታገኙበትም። አያችሁ?

159 ሊደረግ የሚችለው ብቸኛው ነገር፡ አማኞች በሕመምተኞች ላይ እጃቸውን እንዲጭኑ፡ በእግዚአብሔር የተሰጠውን ትዕዛዝ መፈጸም ብቻ ነው። በየዘመናቱ በወንጌል ሪቫይቫሎች ውስጥ፡ ያንን አድርገዋል። እርሱንም፡ “እግዚአብሔር” ብለው ጠርተውታል።

160 አብርሃም ብዙ ምልክቶችን አይቷል። ሆኖም ሰዶም ከመቃጠሏ ጥቂት ቀደም ብሎ፡ አብርሃም የመጨረሻውን ምልክት ያየበት ጊዜ መጣ፡ ያም እግዚአብሔር ራሱን በሰው አምሳል የገለጠበት ጊዜ ነበረ። ይህንን ታምናላችሁን? ኢየሱስ ይህ እንደሚደገም ተናግሯልን?

161 አሁን፡ እዚህ ያላችሁት ሰንቶቻችሁ… በሬዲዮም፡ ወይም በመላ ሀገሪቱ በሰልክ የምታደምጡን፡ አሁንም በማዳመጥ ላይ ካላችሁ፡

እነዚህን መሃረቦችም የያዛችሁት፡ አሁን ለጸሎት ተዘጋጁ፡ ጸልዩም። አሁን፡ እግዚአብሔር ምን ማድረግ እንዳለበት እኔ ልነግረው አልችልም። አይ፡ ይህንን ለመሞከር እንኳ ከእኔ ይራቅ። እርሱ ፍጹም ሉዓላዊ ነው፥ የሚፈልገውን ያደርጋል። ማድረግ የምችለው መታዘዝና እርሱ የሚለውን ብቻ መናገር ነው ።

162 እነሆ አሁን በየግድግዳው ዙሪያ ቆመዋል፡ በተጣበበ ሁኔታ፡ ተጨናንቀዋል። "ይህ መሰህብ ምንድን ነው፡" በሚሉት ቃላት ላይ እግዚአብሔርን ልንጠይቅ እንችል ይሆን? እግዚአብሔር በመካከላችን እንደገና ቢንቀሳቀስ (ምናልባት እዚህ አዲስ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ)፡ በመካከላችንም ቢንቀሳቀስና የተባረከውን ፊቱን በመካከላችን ቢያሳየን፡ መንፈሱ እዚህ መኖሩን ቢያሳየን፡ እርሱ ትናንት፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው መሆኑን ቢያሳየን፡ ማለትም እያንዳንዳችን (ከነዚህ ከሁለቱ ብርቱ መልእክቶች በኋላ) እንዲሁ መሆኑን ማመን እንችል ይሆን? ታደርጉታላችሁን? እሺ።

163 እንግዲህ፡ የጸሎት መሰመር ከመጥራት ይልቅ፥ ሞቃት፡ የተጨናነቀ፡ በግድግዳው ላይ የተጠጋ ነው። የጸሎት መሰመሬን ለመጥራት፡ **ወደዚህ** ዙሪያዬን ብመለከት፡ ልታደርጉት አትችሉም፥ ተመልከቱ፡ በዚያ ቆመዋል። **በዚህ** መንገድ እንዳልጠራ? ሕመምተኞቻችሁ፡ ቃሬዛዎቻችሁ፡ ሌላው ነገር ሁሉ፡ ሞልቷል፥ ልታደርጉት አትችሉም። ስለዚህ እናንተ ባላችሁበት ተቀምጣችሁ፡ እግዚአብሔርን እመኑ። የጸሎት ካርድ ካላችሁ፡ በደንብ ያዙ፡ መልካም ይሆናል። በመሰመር በኩል ማለፍ ከፈለጋችሁ ወደ እናንተ እንመጣለን። ሆኖም በመሰመር ማለፍ የለባችሁም።

164 ባለፈው እሁድ ምሽት፡ ያ አቶ ሸፐርድ፡ በምንም መሰመር አላለፈም። የጸሎት ካርድ ነበረው ብዬም አ—አላሰብም። አቶ ሸፐርድ ዛሬ ማታ እዚህ አለ? የት ነው ያለው? እዚህ አለ? በሰተጀርባ በኩል አለ። አቶ ሸፐርድ፡ የጸሎት ካርድ ነበረዎት? አልነበረዎትም? አልነበረውም። ዛሬ ማታም፡ እንደገና እዚያው ተቀምጧል። ያ ለወንድም ሸፐርድ፡ መሆን ያለበት ጥሩ ቦታ ነው።

165 በዚያ መገኘት ብቻ ሳይሆን፡ እምነት ብቻ ይኑራችሁ። ምክንያቱም፡ አንዲት ሴት ልብሱን እንደዳሰሰችውና እርሱም እንደተነካ፡ አስታውሱ። እርሱም ትናንት፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው። እና በዕብራውያን ሰዎች መልእክት፡ በአዲስ ኪዳን ውስጥ፡ ዛሬም "በድካማችሁ ስሜት ሊነካ የሚችል" ሊቀ ካህናት እርሱ እንደሆነ ይናገራል። ይሄን ታምናላችሁ? እንግዲያውስ እምነት ይኑራችሁ! አትጠራጠሩ። እመኑት፡ ይፈጸማል። ካመናችሁ፡ የለመናችሁትን ሁሉ—መቀበል ትችላላችሁ። ነገር ግን ማመን አለባችሁ። ታደርጉታላችሁ? ሁላችሁም ታምናላችሁ? አሁን ሰንቶች ታምኑታላችሁ? እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

166 ማን ማን እንደሆነ አላውቅም። ከእናንተ መካከል ማንንም አላውቅም። ስለ እናንተ ማወቅ የእኔ ጉዳይ አይደለም። እነዚህን ነገሮች ማወቅ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። ካመናችሁ ግን እርሱ ያደርገዋል። አሁንስ ታምናላችሁን?

167 አሁን፡ የተወደድክ አምላክ ሆይ፡ እኛ በእርግጥ እሽሩሩ መባል፡ እና መቅበጥበጥ የሚያስፈልገን፡ የተዳቀልን ክርስቲያን ህዝብ አይደለንም ልንሆንም አይገባም። ጌታ ሆይ፡ አንተ እንዲህ ዓይነት የለህም። አንተ ጠንካራ

አማኞች አሉህ። የእግዚአብሔር መገኘት የሰውን ልብ እሳት ያደርጋልና። ልክ እንደ አብርሃም፡ እርሱ እግዚአብሔርን አመነ። አንተም ራስህን ለእርሱ ገለጥክለት፡ ተገለጥክለትና ምልክት አሳየኸው፡ እርሱም እመነህ። ሰውነቱን ወደ ወጣትነት መለሰከው፡ የሰውነቱ አካል የነበረችውን፡ የባለቤቱን ሰውነትም፡ እንዲሁ። ከዚያም አዲሱ ልጅ፡ የተሰፋው ልጅ መጣ።

168 እግዚአብሔር ሆይ፡ በዚህ ዘመን ተመሳሳይ ነገር እንደሚሆን ቃል ገብተሃል። ይህን ቃል እንድታረጋግጥ እጸልያለሁ። እና በአህዛብ ዓለም ፍርድ ከመውረዱና፡ ሰዶምም ከመቃጠሏ በፊት እንደሆነው፡ አሁንም በሰዶም እንደነበረው እንደሚሆን፡ በዚያው ቃል ኪዳን ላይ በትክክል እንነጋገራለን። ስለዚህ በአሕዛብ ዓለም ላይ ፍርድ ሊወርድ ተዘጋጅቷል፡ አይሁዶችም በመከራው ዘመን፡ በያዕቆብ መከራ፡ በዳንኤል ሰባ ሳምንታት ቀጣይነት ውስጥ ሌላ ሦስት ዓመት ተኩል አላቸው። ሆኖም፡ የአሕዛብ ቀናት ተቆጥረዋል፡ የምንሄድበት ጊዜ ደርሷል። አንተም ያንን ምልክት ሰጥተሃል፡ አሁንም እንደሚሆን ተናግረሃል። ይሁንልን፡ አምላክ ሆይ። እነሆ፡ እኛ በእጆችህ ውስጥ ነን፡ እንደወደድክ አድርገን። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

169 አሁን አትደናገጡ። ብደናገጥ ኖሮ ምን ይሆን ነበር? አሁን፡ በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ላይ መታመን ያለበትን አንድ ነገር እዚህ እያደረግኩ ነው። ግን ይህንን የማደርገው ለምንድነው? እርሱ እንደሚሆን ስለተናገረ። አለቀ። እርሱ ራሱ እንደዚያ ካደረገ፡ በፊታችሁ እንደዚያ ካረጋገጠ፡ ታዲያ፡ በእርሱ ማመን አትችሉምን? እንዴታ። አሁን እምነት ይኑራችሁና እመኑ።

እስኪ መንፈስ ቅዱስ ወዴት እንደሚመራ፡ ምን እንደሚያደርግ ለማየት፡ ዙሪያዬን ልቃኘው። ምን እንደሚያደርግ አላውቅም፡ ያ የእርሱ ፈንታ ነው። እምነት ብቻ ቢኖራችሁ ግን፡ "ለሚያምኑ ሁሉ ይቻላል፡" እመን ብቻ። ሁላችሁም ያንን ታምናላችሁ፡ እጃችሁን አንሱና "አምናለሁ፡" በሉ። [ጉባኤው፡ "አምናለሁ" አለ።—አርታዒ።] በሙሉ ልቤ፡ አምናለሁ።

170 አሁን ትክክል መሆኑን ለእናንተ ለማረጋገጥ፡ ሦስት ጊዜ በተከታታይ ቢያደርገው፡ ሶስት እንደ ምስክር ይሆናል። የትም ብትሆኑ፡ ማንኛችሁም ብትሆኑ ግድ የለኝም፡ እምነት ብቻ ይኑራችሁና እመኑ። አሁን፡ ወዲያና ወዲህ አ—አትበሉ። **በዚህ** በኩል።

171 የምትጸልዪው፡ እመቤት፡ እኔ አላውቅሽም። ባለሽበት ብቻ ተቀመጪ፥ መምጣት የለብሽም። እኔ አላውቅሽም፡ ሆኖም በእጅሽ ላይ፡ ወይም በእቅፍሽ ላይ አንዲት ህጻን ሴት ልጅ ይዘሻል። እኔ ለአንቺ ፍጹም እንግዳ ነኝ። ያቺም ህጻኗም ደህና ናት፡ ጤናማ ትመስላለች። ቆንጆ ልጅ ናት፡ ቀይ-ጠጉር ያላት ታናሽ ልጅ። እዚህ እሷን እያየኋት ነው፡ አካል ጉዳተኛ ወይም ሌላ ነገር አትመስልም። ችግሯ ምን እንደሆነ አላውቅም። ምናልባት ለልጅቷ ላይሆን ይችላል፥ ምናልባት ለአንቺ ሊሆን ይችላል። ግን ከልጅቷ ጋር ተቀምጠሽ ስትጸልይ፡ በአጋጣሚ አየሁሽ። ኢየሱስ ለሴቲቱ፡ "ውሃ አጠጪኝ" እንዳላት ሁሉ፡ መንፈስሽን ለመያዝ፡ አንድ ደቂቃ ላናግርሽ እፈልጋለሁ፡ አየሽ፡ እንደው አንድ ሰው ለ—ለማወቅ ብቻ። እዚህ የተቀመጡት ወንድም ብራያንትና ሌሎችም፡ እዚህ የተቀመጡትን እነዚህን ሰዎች አውቃቸዋለሁ። ምናልባት፡ እነርሱም እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡ አንቺ ግን እንግዳ ነበርሽ።

172 የእግዚአብሔር ነቢይ እንደሆንኩ ታምኛለሽን? ዛሬ ማታ የሰማሽው ይህ እውነት መሆኑን ታምኛለሽን? አሁን፡ እግዚአብሔር ያደረግሽውን ነገር ቢገልጥልኝ፡ ወይም ማድረግ የማይገባሽን ያደረግሽውን ነገር፡ ወይም በአንቺ ላይ ያለውን ችግር፡ ወይም ፍላጎትሽ ምን እንደሆነ ቢገልጽልኝ፡ እውነት መሆኑን ወይም አለመሆኑን ታውቂያለሽ። አይደል? እርሱም ይህንን ካደረገ፡ እርሱ ትናንት፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው መሆኑንና፡ ያም በቅዱስ ሉቃስ 17፥30 ላይ ያለው መገለጡን ቃሉን ያረጋግጥልናልን? ይህንን ታምኛለሽን?

173 አሁን፡ እንግዳ መሆናችንን ሴቲቱ እጇን በማውጣት ተሰማምታለች። አላውቅሽም፡ ነገር ግን የአንድን ሰው መንፈስ ለመረዳት፡ እየሞከርኩ ነው። በጣም ብዙ ሰዎች እየሳባችሁኝ ነው። አሁን፡ ይህንን በሙሉ ልብሽ እመኚ።

አሁን፡ ይህ ለትንሿ ሴት ልጅ ነው። ለአንቺ አይደለም። አንቺም ጭንቀት አለብሽ፡ የሚያስጨንቅሽ ግን ጭንቀቱ አይደለም። በልብሽ ውስጥ ያለው ታላቅ ነገር ያቺ ታናሽ ሴት ልጅ ናት። እግዚአብሔር እሱ ምን እንደሆነ ሊነግረኝ እንደሚችል ታምኛለሽን? ታምኛለሽን? ይህ ይረዳሻልን፡ ታዲያ ታምኛለሽን? የአንጎል ጉዳት ነው። ልክ ነው? አሁን እጅሽን በትንሿ ልጅ ራስ ላይ ጫኚ፥ እጅሽን።

174 የተወደድክ አምላክ ሆይ፡ አንተ፡ "ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል። እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ፡ እነርሱም ይድናሉ" ብለሃል። ይህች ሴት አማኝ ናት። እጇ በልጅቱ ላይ ነው። ትድን ዘንድ ፈቃድህ ይሁን። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ይህንን ጸሎት አቀርባለሁ። አሜን።

175 አሁን፡ ሁላችሁም ታምናላችሁን? ማመን ቢቻልሽ፡ ሁሉ ይቻላል። ያለጥርጥር!

176 አጠገቧ የተቀመጠችውን እመቤት አውቃታለሁ፡ ነገር ግን እሷ በቅንነት ወደዚህ እየተመለከተች ነው። ስሟን ማስታወስ አልችልም፡ ነገር ግን... ለአንድ ደቂቃ ብመለከታት፡ አውቀዋለሁ። ሆኖም ሴቲቱን በመልክ አውቃታለሁ፡ ነገር ግን ችግርሽ ምን እንደሆነ አላውቅም። ታምኛለሽ እ... አምላክ ያንቺ ችግር ምን እንደሆነ እንዲያሳውቀኝ ታምኛለሽን? እ... ይጠቅምሽ ይሆን? የስኳር በሽታ አለብሽ። አሁን፡ ያ ትክክል ከሆነ፡ እጅሽን አንሺ። ያለጥርጥር!

177 በአጋጣሚ... በአጠገብሽ የተቀመጠችው እመቤት፡ ተመሳሳይ ችግር አለባት። እሷ እንግዳ ናት። ሌላኛዋ እመቤት ለአካል ጉዳተኛ ልጅ፡ እየጸለየች ነው። በሙሉ ልብሽ ካመንሽ፡ እግዚአብሔር ይሰጥሻል።

178 እዚህ ጀርባ በኩል አንድ ሰው አለ። እዚያ የተቀመጠው ሰው፡ ሲጋራ ማጨስን ለማቆም እየታገለ ነው። እግዚአብሔር ይህንን ከአንተ እንደሚያስወግደው ትምናለህ? በጣም ጥሩ። አምነሃል? በል ተቀበል። ይህንን ሰው በሕይወቴ አይቼው አላውቅም።

179 እዚህ አንድ ሰው አለ። እንደ ቃሬዛ፡ ወይም ወንበር ባለው ነገር ላይ የተኛውን በዚህ ሰው ላይ የተንጠለጠለውን ያንን ጥቁር ጥላ አያችሁ? እርሱ እየሞተ ነው። በጥላ አጥሎበታል። ካንሰር አለበት። ይህንን ሰው አላውቀውም፡ አይቼውም አላውቅም። እግዚአብሔር ስለ አንተ ሁሉንም ያውቃል። ይህ እውነት ነው፡ ጌታዬ። እግዚአብሔር ስለ አንተ አንድ ነገር ሊነግረኝ እንደሚችል ታምናለህ? ፈውስህን ለመቀበል ይረዳሃልን?

[ያ ወንድም: “አዎ: አምናለሁ” አለ።—አርታዒ።] በአንድ ወዳጅህ ነው ወደዚህ የመጣኸው። ነገር ግን የአካባቢው ሰው አይደለህም: ሰዎች ዓሳ የሚያጠምዱበት ትልቅ ውኃ ባለበት አካባቢ ነው የምትኖረው። አዎ: አልባኒ: ኬንታኪ። ትክክል ነው። እመን: ተፈውሰህ: ወደ ቤትህ መመለስ ትችላለህ። እንደጠፋ እመን። ካመንክ! ማመን አለብህ: ላንተም እንደተደረገ እመን። ታምናለህ?

180 አንተ: ከቴነሲ የመጣኸው: አሰም ያለበት ወንድ ልጅ አለህ። እዚህ የለም: ነገር ግን እርሱ እንደሚድን ታምናለህ? እንግዲያውስ በእጅህ ያለውን: ያንተ... መሃረብህን ውሰድና: ለእርሱ ሰጠው። ካመንክ እርሱ ይድናል።

181 ከዶክተር ቬይል ፊት ለፊት ተቀምጣ: የምታለቅሰው እመቤት። እሷም: ጥላ አጥሎባታል: ጥቁር ጥላ። ሴቲቱን በህይወቴ አይቻት አላውቅም: ነገር ግን ካንሰር አለባት። ለእሷ የሆነ ነገር ካልተደረገላት ትሞታለች። እንደሚፈውሰሽ ታምኛለሽ: እመቤት? ትችያለሽ? ካመንሽ: እንግዲያውስ ፈውሰሽን ውሰጂ።

182 ከበስተጀርባዋ መሃረቧን በአፏ ላይ ይዛ የተቀመጠች አንዲት እመቤት አለች። እሷም የጨጓራ ቁስለት አለባት: ታማለች። ራስሽን-የመሳት: የማየት መከልከል: የመውደቅ ሁኔታዎች እያጋጠሙሽ ነበር። አንድ ሰው ወደዚህ አምጥቶሻል። በተጨማሪ የሴት ችግርም አለብሽ። ካመንሽ: ወደ ቤትሽ ሂጂ: ደህና ሁኚ።

183 አንተ: ወጣቱ: እዚህ ልክ ከፊቴ ተቀምጠህ፥ የምትመለከተኝ: እንግዳ ነህ። ፖርቶሪካዊ ወይስ ሌህ: ምንድነው? አዎ: ማለቴ: ማለቴ: እኔ ለአንተ እንግዳ ነኝ። ይሄን ታውቃለህ፥ ከሀገሬ እንኳን አይደለህም። ነገር ግን እግዚአብሔር የልብህን ምኞት እንደሚሰጥህ ታምናለህ? ፍላጎትህ ምን እንደሆነ ከነገርኩ: ትቀበለዋለህን? የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት እየፈለግክ ነው። እውነት ነው። መንፈስ ቅዱስን ተቀበል: ወንድሜ።

184 እዚህ ጋር አንድ ጥቁር ሰው ተቀምጧል: በልቡ ላይ ሸክም አለበት። ይህ ለሚስቱ ነው። በርግጥ: እርሷ እዚህ የለችም። እግሯ ጋር ችግር አለባት። እንደሚፈውሳት ታምናለህ? ታምናለህ? እዚህ እንግዳ ነህ። ከባሕር ማዶ ነህ። ከጀማይካ ነህ። እግዚአብሔር ማን እንደሆንክ ሊነግረኝ እንደሚችል ታምናለህ? ሚስተር ብራዲ። ታምናለህን? ኢየሱስ ክርስቶስ ትላንት: ዛሬ: እና ለዘላለም ያው እንደሆነ ታምናለህ።

185 **እዚህ** ማዕዘን በኩል ከበስተጀርባ: ከወይዘሮ ራይት አጠገብ የተቀመጠችው እመቤት: በልቧ ላይ ሸክም አለባት። ለሴት ልጇ እየጸለየች ነው። ቀዶ ጥገና ልታደርግ ነው። ስለ እሷ: በሙሉ ልብሽ ታምኛለሽን? እንድታምን ካደረገሻት ቀዶ ጥገናው አያስፈልጋትም። እኔ መፈወስ አልችልም።

186 በስተጀርባ ባለው የሕፃናት ክፍል ውስጥ: የእግዚአብሔር መንፈስ: አንድ መልአክ: ብርሃን በክፍሉ ውስጥ ሲንቀሳቀስ አያለሁ። በአንዲት ወጣት ሴት ላይ ነው: እሷ መንፈሳዊ ችግር አለባት መቅበዝበዝ ላይ ናት። በሆነ መንገድ: ያችን ወጣት ሴት: የማውቃት ይመስለኛል። እሷም የማኅፀን ችግር አለባት። አዎን። ስሟ ወይዘሮ ዌስት ነው: ከአላባማ: ወይዘሮ ዴቪድ ዌስት ናት። እመኚ፥ እግዚአብሔር ይሰጥሻል።

187 “የሰው ልጅ በሚገለጥበት በዚያ ዘመን፡ ብርሃን ይሆናል።” ይህ ትናንት፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ካልሆነ፡ ሌላ ነገር አላውቅም። ይሄን ታምናላችሁ? ለሚያምኑ ሁሉ ይቻላል።

188 አሁን በመላ አገሪቱ በማይክሮፎኖች በኩል የምትሰሙና፡ በዚህ ተበርናክል ውስጥ ያላችሁ ሁሉ፡ ሰንቶቻችሁ እጆቻችሁን አንስታችሁ፡ “እማኝ ነኝ” ትላላችሁ? አሁን፡ እናንተ በየቦታው ያላችሁ፡ እዚህ ያሉት ሁሉ፡ እጆቻቸውን አንሥተዋል። በመላ አገሪቱ፡ በዚያ በኩል ያላችሁትም፡ ያለጥርጥር፡ እጆቻችሁን አንሥታችኋል። አሁን አይኖቻችሁን ጨፍኑ፡ አጠገባችሁ ባለው ሰው ላይ እጆቻችሁን ጫኑ። እጆቻቸውን ያዙ። ትከሻዎቻቸው ላይ አድርጉ። መሃረቦቹ ላይ እጆቼን አድርጌአለሁ። ዛሬ የተደረገውን ተመልከቱ! አሁን የተደረገውን ተመልከቱ።

የተቀደሰ ፊቱን አይተን
በመለኮታዊ ፍቅር የበራ፥
የጸጋው ተካፋዮች ብጹእን፡
በዘውዱ ላይ እንደ ዕንቁዎች የምናበራ።

አሁን ጸልዩ። በየትኛውም ቦታ፡ እንጸልይ።

189 አምላክ ሆይ፡ ሰዓቱ ደርሷል። ይህ ምን ማለት ነው? እግዚአብሔር ቃሉን ሲፈጽም ነው! ጌታ ሆይ፡ መሰህቡ ምንድነው? እግዚአብሔር ቃሉን ሲፈጽም ነው። በሰልክ አማካኝነት፡ በመላ ሀገሪቱ፡ ከአንዱ የባሕር ዳርቻ ወደ ሌላኛው ከሰሜን ወደ ደቡብ፡ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ፡ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች፡ እጃቸውን የተጫጫኑት ይህ ምንድን ነው? እዚህ ከውጭ አገራት፡ ከብዙ ክልሎች፡ ከሜክሲኮ፡ ካናዳ፡ እጆቻችንን እርስ በእርሳችን ጭነናል። እግዚአብሔር ቃሉን እየፈጸመ ነው!

190 ይህ ሰው በመንፈስ ቅዱስ እዚህ ቆሞ ሰምዖን ጴጥሮስ ላይ እንደሆነው ማድረግ የቻለው እንዴት ነው፡ “ሰምህ ሰምዖን ነው፡ የዮና ልጅ ነህ”?

“ሂጂና ባልሽን ይዘሽ ወደዚህ ነይ።”

“ባል የለኝም።”

“እውነት ተናገርሽ፡ አምስት ባሎች ነበሩሽና።”

191 እንዲህ አለችው፡ “መሲሑ ይሄን ሊያደርግ እንደሚመጣ አውቃለሁ፡ ግን አንተ ማን ነህ? ”

እርሱም፡ “እኔ እሱ ነኝ” አላት።

192 አንተ ትናንትናም፡ ዛሬም፡ ለዘላለም ያው ነህ። እንደ ተሰፋ ቃልህ፡ “እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተም ታደርጋላችሁ። እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፡ ከዚህ በላይ ታደርጋላችሁ።” “እና፡ እነሆ፡ በመጨረሻው ዘመን፡ ነቢዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ፡ እርሱም የሰዎችን አስተሳሰብ ይለውጣል፡ የልጆችን ልብ ወደ ሐዋርያት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ይመልሣል።” “ሲመሽ ብርሃን ይሆናል።”

193 ይኸው፡ ታላቁ የሰማይ አምላክ ሆይ! ጊዜው አሁን ነው! እጆች በህዝቡ ላይ ናቸው።

194 ሰይጣን፡ ተሸንፏሃል። ውሸታም ነህ። እነሆ፡ እንደ እግዚአብሔር አገልጋይ፡ እና እንደ አገልጋዮች፡ የእግዚአብሔርን ቃል እንድትታዘዝና፡ ከሕዝቡ እንድትወጣ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዝሃለን፡ “በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፡” ተብሎ ተጽፏልና።

195 ህዝቡም ሁሉ ነጻ ይሁን። ይሁንልን፡ አምላክ ሆይ። በቀራንዮ ተራራ ላይ በነበረው ያ መሰህብ፡ በዚያን ቀን ሕመምንና በሽታን ሁሉ፡ የሰይጣንንም ሥራ ሁሉ ያሸነፍክ የሰማይ አምላክ ነህ። አንተ አምላክ ነህ። ህዝቡም በቁስልህ ተፈወሰ። ነፃ ናቸው። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

196 አምላክ ሆይ፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ባለበት፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ቅባት በሕዝቡ ላይ ባለበት፡ እርሱም ቃል የገባቸው ታላላቅ ምልክቶች እየተፈጸሙ ባሉበት፡ ምድሪቱም እየተንቀጠቀጠች፡ የምድር መንቀጥቀጦች እየሆኑ ባሉበት፡ እርሱ የተናገራቸው፡ ታላላቅ ምልክቶችና፡ ቅዱስ ቃላት እየተፈጸሙ፡ የምሽቱም ብርሃን እያበራ፡ መሃረቦች ሁሉ እዚህ ተቀምጠዋል። ከምሥራቅ፡ ከምዕራብ፡ ከሰሜንና፡ ከደቡብ ያሉትን እነዚህን እማኞች በሙሉ በመወከል፡ አካሌን በእነዚህ መሃረቦች ላይ እዘረጋለሁ፥ ለሰይጣንም፡ “በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እነዚህ የተጫኑባቸውን ታማሚዎች ሁሉ ልቀቅ” እላለሁ፡ ለእግዚአብሔር ቃል ክብርና ምስጋና ይሁን። በእግዚአብሔር ቃል ስም፡ በናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

197 አሁን፡ በጸጥታ፡ በማስተዋል፡ በንቃት፡ በጤናማ አእምሮአችሁም፡ እንደ እማኞች፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ሁሉን ከሚችል ከእግዚአብሔር ዘንድ ፈውሳችሁን እምናችሁ ትቀበላላችሁን? ካመናችሁ፡ እጆቻችሁን አንሡ። በየቦታው ያላችሁ ሁሉ፡ ባላችሁበት እጆቻችሁን አንሡ። እዚህ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ሰው፡ እኔ እንደማየው ሁሉ፡ እጃቸውን ወደ ላይ ከፍ አድርገዋል፥ በውስጥ፡ በውጭ፡ በመስኮቶች አጠገብ፡ በደጆች ላይ፡ በሕፃናት ክፍል ውስጥና፡ በሁሉም ቦታዎች ላይ፡ ሰዎች እጆቻቸውን አንሥተዋል። ተቀብለውታል ። ሰይጣን ተሸንፏል! የኢየሱስ ክርስቶስ ቍስል ፈውሷችኋል፡ የኢየሱስ ክርስቶስም መገኘት እርሱ ዛሬ ሕያው መሆኑን፡ የገባውን ተስፋ ሁሉ ለመፈጸም ምንጊዜም የሚችል መሆኑን እውነታውን ያረጋግጣል። አሜን! አምነዋለሁ። እናንተስ? [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።]

198 አሁን በእግሮቻችን እንቁም። በጌታ በኢየሱስ ስም፡ የተደረገውንና የተባለውን ነገር ሁሉ በመቀበል፡ በሙሉ ልባችን እንወደዋለን። በውስጣችን ባለው ኃይል ሁሉ እንወደዋለን። አሁን ዛሬ ማታ ወደየቤቶቻችሁ ስትሄዱ፡ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን። መንፈስ ቅዱስ ከሌላችሁ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ይስጣችሁ።

199 እዚህ ያላችሁ፡ ወንዶች፡ ሴቶች፡ ወንድ ልጆች፡ ወይም ሴት ልጆች፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያልተጠመቃችሁ ሁሉ፡ ልብሶችና ገንዳው፡ ተዘጋጅተዋል። ዛሬ ሊደረግ የሚችለውን ነገር ለነገ አታስተላልፉ። ነገ በጣም ዘግይቶ ሊሆን ይችላል። “ለቀኑ፡ ክፋቱ፡ ይበቃዋል።” ቆመው የሚጠብቁ፡ ሰባኪዎች አሉ፡ ልብሶችም ተዘጋጅተዋል። ምንም ሰበብ የለም። እየጠበቃችሁ ነው? ከሆናችሁ፡ እመኑ። እንዴትም ብትጠመቁ፡ በመርጨት፡ በማፍሰስ፡ ምንም ይሁን ምን፡ እሱ ስህተት ነው። ብርሃኑ መጥቷል። ኑ፡ እመኑ፡ ተጠመቁም።

200 መንፈስ ቅዱስ የሌላችሁ ሁላችሁም፡ እርሱ፡ በአምላካዊ ኃይልና ፍቅር ቃል በገባላችሁ መሠረት፡ በእርሱ አዲስ ፍጡር ያደርጋችሁ ዘንድ፡ መንፈስ ቅዱስን ትቀበሉ ዘንድ ፈቃዱ ይሁን። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

201 አሁን፡ እስከሚቀጥለው እሁድ ጠዋት ዘጠኝ-ተኩል ላይ፡ ከዓመታት በፊት እንዘምር የነበረውን ይህን መዝሙር እንዘምር፥

የቤተሰብ ጸሎት አትርሱ፡
ኢየሱስን በዚያ እንድትለብሱ፥
ሸክማችሁን ይወስደዋል እሱ፡
የቤተሰብ ጸሎት አትርሱ።

አሁን አብረን እንዘምር።

የቤተሰብ ጸሎት አትርሱ፡
ኢየሱስን በዚያ እንድትለብሱ፡
ሸክማችሁን ይወስደዋል እሱ፡
እነሆ፡ የቤተሰብ ጸሎት አትርሱ።

202 አሁን እንደገና ስንዘምረው፡ አጠገባችሁ ካለው ተጓዥ ጋር እጅ ለእጅ ተጨባበጡ፡ እያችሁ፡ ስንዘምረው።

የቤተሰብ ጸሎት አትርሱ፡
ኦህ፡ ኢየሱስ በዚያ እንድትለብሱ፡
ሸክማችሁን ይወስደዋል እሱ፡
እነሆ፡ የቤተሰብ ጸሎት አትርሱ።

203 አትወዱትምን?

እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ
ቀድሞ ስለወደደኝ
መዳኔንም ገዛው (መሰህቡ ያ ነበር።)
በቀራንዮ ተራራ።

ያው መሰህብ በሳንሴት ተራራ፡ በኔቦ ተራራ፡ በሲና ተራራ፡ በሁሉም የተለያዩ የተራራ ጫፎች ላይ በነበሩት ተሞክሮዎች ላይ ነበረ። እንግዲህ፡ እሺ፡ አሁን እንዘምረው።

እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ
ቀድሞ ስለወደደኝ
መዳኔንም... መዳኔንም ገዛ
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

204 እሱን የምትወዱ ሁሉ፡ “አሜን፡” በሉ። [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።] እንዲሁ ይሁን! አሁን እርሱ ለእናንተ ስላደረገው ነገር ብቻ አስቡ፥ አስቡት፡ ዛሬ ማታ በጠጅ ቤት ውስጥ ልትሆኑ ትችሉ ነበር። ከእግዚአብሔር ምሕረት ርቃችሁ፡ እኔ ሊሆን ይገባኝ እንደነበረው ምናልባት በመቃብር ውስጥ ትሆኑ ነበር። እርሱ ምን አድርጎልሃል? ኦህ፡ እሱን ከመውደድ እንዴት ልንከለከል እንችላለን? ማን ምንም ቢናገር ግድ የለም፡ እርሱ ቀዳሚ ነው።

205 አሁን ለእርሱ እየዘመርን አይናቻችንን ጨፍነን፡ አንገታችንን ዝቅ እናድርግ። መዝሙሮችን ይወዳል፡ መዝሙሮችን። አሁን ለእርሱ እንዘምርለት።

እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ
ቀድሞ ስለወደደኝ
መዳኔንም ገዛ
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

206 በፊቱ ራሳችንንና ልባችንን ዝቅ አርገን፡ ዓይኖቻችን ላዩት፡ ጆሮዎቻችን ለሰሙት፡ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ለተጻፈው፡ ዛሬም ለእኛ ለሆነው ለተሰፋው ቃል ምስጋና ይሁን። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

207 ዛሬ ማታ አንድ እ—እንግዳ በመካከላችን አለ፡ ኔድ አይቨርሰን፡ ቀደም ሲል የፕሪስቢቴሪያን ሰባኪ የነበረ፡ ወንድማችን። አባቱ፡ ወንድሞቹ፡ የፕሬስባይቴሪያን አገልጋይ ናቸው። እርሱ፡ ዛሬ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እንደገና፡ እንደተጠመቀ፡ ተረድቻለሁ። እርሱ አገልጋይ ነው፡ በዚያም ላይ በጣም የተዋጣለት ነው። አሁንም የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደሆነ ስለማምን፡ ወደየቤቶቻችሁ ስትሄዱ፡ በጉባኤ ላይ የእግዚአብሔርን በረከት እንዲጠይቅ እጋብዘዋልለሁ።

208 ወንድም አይቨርሰን፡ ለመጸለይ ራሳችንን ዝቅ አድርገን ሳለ፡ ወዲህ ና። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድሜ።

65-0725E ተራራው ላይ ያለው መሰህብ ምንድን ነው?
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤሰ.ኤ

AMHARIC

©2026 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org